አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን
ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ

(በከምባታ ጠምባሮ ዞን ሀደሮ ጡንጦ ወረዳ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)

በ

ታገሠ ሙላቱ

ሰኔ 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ
# (በከምባታ ጠምባሮ ዞን ሀደሮ ጡንጦ ወረዳ የመንሥት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን፣

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለተግባራዊ ሥነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

ታገሠ ሙላቱ


ሰኔ 2015 ዓ/ም

አዲስ አበባ

# የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ
# (በከምባታ ጠምባሮ ዞን ሀደሮ ጡንጦ ወረዳ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍልየድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

## ለተግባራዊ ሥነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

**በ**

**ታገሠ ሙላቱ**

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

## ማረጋገጫ

የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ (በከምባታ ጠምባሮ ዞን ሀደሮ ጡንጦ ወረዳ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት) በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም ____________________________

ፊርማ____________________________

ቀን ____________________________

# ምሥጋና

በቅድሚያ ይህንን ሥራ አስጀምሮ ላስፈጸመኝ ለእግዚአብሔር ክብርና ምሥጋና ይገባዋል፡፡ በመቀጠል ጥናቱ ተጀምሮ ለፍጻሜ እስከበቃ ድረስ ረቂቆቹን በማንባብ አስተያየት በመስጠትና በማቃናት ያለመሰልቸት ድጋፋቸውን በመስጠት ጥናቴን አጠናቅቅ ዘንድ ሙያዊ ድጋፋቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ዶ/ር ታደሰ ሲባሞ ያለኝ አክብሮትና ልባዊ ምሥጋና ወደር የለውም፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊውን ትብብር ላደረጉልኝ ትምህርት ቤቶች፣ የቋንቋ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ተማሪዎች ልባዊ ምሥጋና ይድረሳቸው፡፡ ለዚህ ጥናት ዝግጅትና ለሥራዬ መሳካት በተለያየ መልኩ ከጐኔ ሳይለዩ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለዉድ ባለቤቴ ለመምህርት ደመቀች መሎሬ፣ ለሥራ ባልደረቦቼ ለአዳነ ሊሞሬ፣ ለተረፈ ኤርሰዶ፣ ለአሸናፊ ማርቆስ እና ለይስሐቅ አብርሃም ምሥጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

በመጨረሻም ትምህርቱን እንድማር ዕድሉን ላመቻቸልኝ ለትምህርት ሚኒስቴርና ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ልባዊ ምሥጋና አቀርባለሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ አራት የመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አተገባበር ግምገማ መፈተሽ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በዋናነት በመምህራን ላይ ትኩረት ያደረገ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ምልከታ ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም መምህራንና ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ በሀደሮ ጡንጦ ወረዳ የሚገኙ 4 የመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአመቺ ናሙና ተመርጠዋል፡፡ የመማሪያ ክፍሎቹም በዕጣ ናሙና ስልት እንዲመረጡ ተደርጓል፡፡ አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በኢላማዊ ናሙና ተመርጠው በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ አንድ መቶ አስራ ሁለት ተማሪዎች በመረጃ ሰጪነት የተሳተፉት እኩል ዕድል በሚሰጠው በቀላል የዕጣ ናሙና ስልት ነው፡፡ የክፍል ምልከታና የዕሁፍ መጠይቅ ለጥናቱ ተግባራዊ የተደረጉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ናቸው፡፡ የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አተገባበር ተፈትሾ ደካማና ጠንካራ ጐኖቹን በመለየት ጠንካራውን ይበልጥ የሚጐለብቱበትን፣ ደካማው የሚሻሻልበት የመፍትሄ ሀሳብ ተጠቁሟል፡፡ መምህራን የንግግር ክሂል ትግበራውን አሰባስበውና ጊዜ ውስደው የተማሪዎችን በራስ የመተማመን መናገር ፍላጐትን የማይቀሳቅስ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበር ጊዜ ውስደው ሲሰሩ አልታዩም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ግድየለሽነት ሲታይባቸው ተስተውሏል፡፡ ለመናገር የሚፈሩና አይናፋር ተማሪዎችን ጊዜ ወስደው እንዲዘጋጁ የሚያደርግ ተግባር ያልተፈጸመ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡ በመጨረሻም በጥናቱ ከላይ ለተጠቀሱት ችግሮች የሚመለከታቸው የትምህርት ባለድርሻ አካላት መምህራንና ተማሪዎች ምን ምን ማድረግ እንዳለባቸው የመፍትሄ ሃሳቦችን ጠቁሟል፡፡

ማዉጫ ገጽ

ማረጋገጫ ........................................................................................................ I
ምሥጋና ........................................................................................................ II
አጠቃሎ........................................................................................................ III
ማዉጫ ........................................................................................................ IV
የሠንጠረዥ ማውጫ ........................................................................................................ VI
ምዕራፍ አንድ ........................................................................................................ 1
መግቢያ ........................................................................................................ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................................................ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................................................................................ 2
1.3 የጥናቱ አላማ........................................................................................................ 3
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................................................................................ 3
1.5 የጥናቱ ወሰን ........................................................................................................ 4
ምዕራፍ ሁለት ........................................................................................................ 5
ክለሳ ድርሳናት........................................................................................................ 5
2.1 የመናገር ክሂል ፅንሳ ሃሳብ........................................................................................................ 5
2.2 የመናገር ክሂልን የማስተማር አላማ........................................................................................................ 5
2.3 የመናገር ክሂልን የመማር አስፈላጊነት ........................................................................................................ 6
2.4 የመናገር ክሂል ተግባራት (activities) ባህርያት........................................................................................................ 7
2.5 የንግግር ክሂል ትምህርት የማስተማር ደረጃዎች ........................................................................................................ 8
2.5.1 ቅድመ ንግግር ተግባራት፡-........................................................................................................8
2.5.2 የንግግር ጊዜ ተግባራት፡- ........................................................................................................8
2.5.3 የድህረ ንግግር ተግባራት፡-........................................................................................................9
2.6 የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት ........................................................................................................ 9
2.7 የመናገር ክሂል ሲተገበር የሚያጋጥሙ ችግሮች ........................................................................................................ 15
2.8 የመናገር ክሂል ሲተገበር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማስወገድ የሚጠቅሙ ተግባራት ................ 16
2.8.1 የቡድን ሥራ መጠቀም፡- ........................................................................................................16
2.8.2 ተግባሩን በቀላል ቋንቋ እንዲቀርብ ማድረግ፣ ........................................................................................................16
2.8.3 ፍላጎት ለማነሳሳት ሳቢና አነቃቂ የመወያየ ርዕስ ወይም ተግባር መምረጥ፡-......................17
2.9 በመናገር ክሂል ትምህርት ጊዜ የመምህሩ ሚና ........................................................................................................ 17
2.10 በመናገር ክሂል ትምህርት ጊዜ የተማሪው ሚና........................................................................................................ 18
2.11 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት........................................................................................................ 18
ምዕራፍ ሦስት........................................................................................................ 20
የአጠናን ዘዴ ........................................................................................................ 20

3.1 የጥናቱ ንድፍ ..... 20
3.2 የናሙና አመራረጥ ..... 20
3.2.1.የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ..... 21
3.2.2.የመመሪያ ክፍል ናሙና አመራረጥ ..... 21
3.2.3.የመምህራን ናሙና አመራረጥ ..... 21
3.2.4.የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ..... 21
3.3. መረጃ መሰባሰቢያ ዘዴዎች ..... 22
3.3.1.የክፍል ውስጥ ምልከታ ..... 22
3.3.2.የፅሁፍ መጠይቅ ..... 22
3.4.የመረጃ አተናተን ዘዴ ..... 23
ምዕራፍ አራት ..... 24
4. የውጤት ትንተናና ማብራሪያ ..... 24
4.1 የውጤት ትንተና ..... 24
4.1.1. በቅድመ ንግግር በክፍል ውስጥ አተገባበር የተገኘ መረጃ ትንተና ..... 24
4.1.2. በንግግር ጊዜ የንግግር አተገባበር ዙሪያ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ..... 36
4.1.3. በድህረ ንግግር የንግግር አተገባበር ዙሪያ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..... 45
4.2. የውጤት ማብራሪያ ..... 46
ምዕራፍ አምስት ..... 49
5.ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች ..... 49
5.1. ማጠቃለያ ..... 49
5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች ..... 50
ዋቢ ፅሑፎች ..... 52

**የሠንጠረዥ ማውጫ** **ገጽ**

ሠንጠረዥ 1፡- በጥናቱ የተካተቱ ትምህርት ቤቶች፣ የተማሪዎች እና የመምህራን ብዛት የናሙና መጠን እና የምልከታ ጊዜ መግለጫ....20
ሠንጠረዥ 2፡- በቅድመ ንግግር የክፍል ውስጥ አተገባበር ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ....25
ሠንጠረዥ 3፡- ለመምህራን ከቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ የተሰባሰበ ቅድመ ንግግር የሚመለከት መረጃ....29
ሠንጠረዥ 4፡- በቅድመ ንግግር የመናገር ክሂል ተግባራት የክፍል ውስጥ አተገባበር የተማሪዎች ምላሽ ትንተና....33
ሠንጠረዥ 5፡- በንግግር ጊዜ ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና....37
ሠንጠረዥ 6፡- የንግግር ጊዜ ተግባርን አስመልክተው መምህራን የሰጡት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ትንተና....40
ሠንጠረዥ 7፡- የንግግር ጊዜ ተግባራትን በሚመለከት ለተማሪዎች ከቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና ....42
ሠንጠረዥ 8፡- በድህረ ንግግር አተገባበር ዙሪያ በክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ....45

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ንግግር የዕለት ተእለት ሕይወት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው መልዕክት በአግባቡ ለአድማጭ ማስተላለፍ የሚያስችል ክሂል ነው፡፡ ነገር ግን በአብዛኞቹ ተማሪዎች ይህ ሲሆን አይታይም፡፡ የንግግር ክሂል የማስተማር ሥነ ዘዴ በክፍል ውስጥ ያለው ሂደት በተለይ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የንግግር ክሂልን የሚያዳብሩት ሁኔታ ትኩረት የሚሰጥ ነው በማለት Harmer (1991)ገልፀዋል፡፡

ንግግር ሰውን ከእንስሳት ከለዩት ክስተቶች አንዱና ዋነኛው ሲሆን የፅሁፍ ጥበብ ከመምጣቱ በፊት ጀምሮ ለረጅም ዘመናት ከሰው ልጅ ጋር አብሮ ኖሯል፡፡ ይሁን እንጂ ከንግግር እጅግ በጣም ዘግይቶ ከመጣው ከፅሑፍ ጋር ሲነፃፃር የሚሰጠው ግምት አነስተኛ ነው፡፡ ክሂሉ ትኩረት ያላገኘ በመሆኑ MCDonough and Shaw(1995) ለፅሁፍ በተለይም ሊነበብ ለሚችል ሥነ-ፅሁፍ ከፍተኛ የሆነ ግምትና ክብር ሲሰጥ ንግግርን ማስተማር ግን ብዙን ጊዜ ተራ የንግግር ቋንቋ ማስተማር ተደርጐ ስለሚታሰብ ዝቅተኛ ግምት ይሰጠዋል፡፡ የሰዎች ማንነት አብዛኛውን ጊዜ የሚለከው ከሌሎች ክሂሎች ይልቅ በንግግራቸው ስለሆነ ንግግር ጥበብ ነው፡፡ ስለሆነም ለንግግር ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

Bygate (1987:6) በበኩላቸው ንግግር ማስተማር ቸል የማይባል ጉዳይ መሆኑን እንዲህ ሲሉ ያስገነዝባሉ፡፡ ተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት በማዳበር በሚያደርጉት ንግግር ዕለታዊ ተግባሮቻቸውን ማከናወን ይፈልጋሉ፡፡ በንግግራቸውም ማንነታቸው ይለካል፡፡ ንግግር አመርቂ የሆነ ማህበራዊ ትብብር፣ ማህበራዊ ቦታ፣ ሙያዊ ከበሬታ ከመሆኑም በተጨማሪ ቋንቋን ለመማር ለመሣሪያነት በማገልገል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ አተገባበር በማመለከት ከመምህር መሪ የመማር ማስተማር ዘዴ ይልቅ ቡድኖችን በተለያየ መልክ በማዳራጀት እያንዳንዱ ተማሪ የተለያየ ሀሳቦችን በማፍለቅ እርስ በርስ የተሻለ እንዲናገሩ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎቹ ብዙን ጊዜ የሚያጠፉት ሀሳባቸውን ለመረዳት በሚያደርጉት ጥረት ተጠምደው ነው በማለት Bygate (1987፡96) ገልፀዋል፡፡

የንግግር ክሂል ክፍል ውስጥ ሲተገበር በመምህራን በኩል ልዩ ዝርዝር አላማዎች ተነድፈውለት፣ ጠቋሚ ይዘቶች ተመርጠውለት በልዩ ልዩ ማስተማሪያ ዘዴ ተደግፎ

ለተማሪዎች ሊቀርብ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የንግግር ክሂል ሊዳብር የሚችለው እንደ ሌሎች የቋንቋ እውቀቶች ህጎችን በማስተማር ወይም በመናገር ሳይሆን በተግባራዊ ተሳትፎ ነው በማለት (ማረው፣1998) ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ የቋንቋ መምህራን ዋና የሆኑ ማስተማሪያ ስልቶችን በመንደፍ የንግግር ክሂሎታቸውን እንዲያዳብር ማገዝ ጭምር ነው፡፡

Ur (1996፡227) በበኩላቸዉ የክፍል ውስጥ ማስተጋብራዊ ክንውኖች አነሳሽነት ሁልጊዜ በመምህሩ እጅ መውደቅ የለበትም፤ መስተጋብሩ በተማሪዎች መካከል ወይም በተማሪዎችና በማቴሪያል መካከል ሊሆን እንደሚችል በመጥቀስ የቋንቋ ክፍልን ገፅታ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡

ማረው (2003፡105) የመናገር ክሂል የሚዳብረው ህጎችን በማስተማር ወይም በመንገር ሊሆን አይችልም፤ እንደማንኛውም ክሂል የመናገር ክሂል የሚዳብረው በተግባራዊ ተሳትፎ ብቻ ነው፡፡ ተማሪዎች እየፃፉ የመፃፍ ክሂላቸውን እንደሚያዳብሩት ሁሉ እየተናገሩም የመናገር ክሂላቸውን ማሳደግ አለባቸው፡፡ ህፃናት ቋንቋ ሲለምዱ ሌላው (አዋቂ) የሚለውን በማዳመጥና እነሱም መልሰው በማለት ነው፡፡ የመናገር ክሂልም የዚህ መሰል ተሳትፎ ያስፈልገዋል በማለት አብራርተዋል፡፡

ከላይ ከምሁራኑ ሃሳብ የምንረዳው የመናገር ክሂልን ተማሪዎች የሚያጎለብቱት ስለመናገር ክሂል ምንነትና የማስተማሪያ ስልቶችን እያቀያየሩ በመጠቀም ሁሉም ተማሪዎች ተግባራዊ ልምምድ በየጊዜው ማድረግ ሲችሉ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የጥናቱ አቅራቢ ባለው የማስተማር ልምድ ከትምህርት ክፍሉ መምህራን ጋር የልምድ ልውውጥ ባደረገበት ጊዜ የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ሲፈተሽ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንግግር ክሂልን ሲያስተምሩ ተማሪዎችን ስላዳመጡት፣ ስላዩትና ስለተሰማቸው ነገር በንግግር እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ሀሳባቸውን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ መግለጽ አለመቻላቸው እንደ መነሻ ችግር ይታያል፡፡ ተማሪዎች የንግግር ክሂልን በተሻለ መልኩ ለማዳበር ሰፊ ልምምድ፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የሀሳብ ተለጣጣቂነት እና ግጥምጥምነት ወዘተ… ማወቅና ብዙ ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህን አስመልክቶ Byrne (1976) ሲገልጹ ተማሪዎች የመናገር ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ እና ልዩ ልዩ ችግሮች እንዲፈጠርባቸው ምክንያት የሆኑት የግንዛቤ እና ከቋንቋ ችሎታ አነስተኛነት የሚመነጩ ናቸው ብለዋል፡፡ በድሉ (2007፡87) እንደጠቀሱት የመናገር ክሂል አስፈላጊነትን በተመለከተ "አብዛኞቹ ተማሪዎች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁት ጥሩ የንግግር ችሎታ ሳያዳብሩ ነው"፡፡

በመሆኑም ከትምህርት ቤት በኋላ ባለው ህይወታቸው ያለምንም ችግር ሀሳባቸውን በንግግር ለመግለጽ ይቸገራሉ። በራስ ያለመተማመንና መልዕክትን በምክንያትና ውጤት አደራጅተው ያለማቅረብ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው (ቅድስተማሪያም ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፣2006፡ 24)።

የጥናቱ ውጤትም የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ሲታይ በሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረሱን ያመለክታል። ስለሆነም የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ምን ምን የመናገር ክሂል ተግባራትን ይገለገላሉ? የተግባራቱ አቀራረብ በሚመለከት ግንዛቤው አላቸው ወይ? ግንዛቤው ካላቸው እንዴት እየሠሩ ነው? ተግባራቱ በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡስ ምን ምን ችግሮች ያጋጥሟቸዋል? የሚሉትን ጥያቄዎች ፈትሾ ምላሽ መስጠት የጥናቱ መነሻ ሀሳቦች ናቸው።

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በከምባታ ጠምባሮ ዞን በሀደሮ ጡንጦ ወረዳ በተመረጡ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ነው። ጥናቱ የሚያተኮርባቸው ዝርዝር አላማዎች አሉ።

1) የመናገር ክሂል በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመምህሩና የተማሪው ሚና ምን እንደሆነ ማረጋገጥ፣
2) መምህራን የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የታዩ የአቀራረብ ችግሮችን እና የችግሮቹን መንስኤዎች መለየት፣
3) በመናገር ክሂል ተግባራት አቀራረብ ክንውኖች ወቅት ለተከሰቱ ችግሮች የመፍትሄ ሃሳብ ማቅረብ፣

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

- መምህራንና ተማሪዎች የመናገር ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ የተለያዩ ተግባራትን ለይተው በማወቅና በመማር ማስተማሩ ተግባር በቀጣዩ እንዲገለገሉባቸው ያግዛል፣

- መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርትን ሲያቀርቡ አስፈላጊ የሆኑ የንግግር አቀራረቦችን ተከትለው ለተማሪዎቻቸው እንዲያስተምሩ ሊያነሳሳቸው ይችላል፡፡
- መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርትን ሲያቀርቡ አስፈላጊ የሆኑ ሂደቶችን ተከትለው በማስተማር በኩል ግንዛቤያቸው ምን እንደሚመስል ለመገንዘብ፣
- በመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አቀራረብ ለሚታዩ ችግሮች የመፍትሔ ሃሳብ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የተካሄደው በደቡብ ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን በሀደሮ ጡንጦ ወረዳ በሚገኙ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ሥር የሚገኙት ዶንጋ ጡንጦ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ አመለቃ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በሶድቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በሙጉንጃ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነው፡፡ ጥናቱ የሚያተኩረውም በ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ ላይ ሲሆን የዚህ ክፍል ደረጃ መምህራን እና ተማሪዎች የጥናቱ ተተኳሪዎች ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የመናገር ክሂል ፅንሳ ሃሳብ

የመናገር ክሂል ለቃላዊ ተግባቦት ከሚያስፈልጉ የቋንቋ ችሎታዎች አንዱ ሆኖ ከመማሪያ ክፍል ውጭም ሆነ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ራስን ከሌሎች ጋር ለመግባበት የሚያስችል መሳሪያ ነው፡፡ ተስፋዬ (1981፡61) መናገር ሲባል ሀሳብ እንደመጣ መቀበጠር ወይም መለፍለፍ አይደለም፡፡ ስሜት ያፈለቀውን፣ አይን የተመለከተውን፣ በንባብ የተገኘውን፣ ውይይትና ጨዋታ የወለደውን ጉዳይ መነሻ በማድረግ ሀሳብን ለሌላው የማህበረሰብ ክፍል ወግና ሥርዓት ባለው ዘዴ መግለፅና ለማስደመጥ መሞከር ነው፡፡ አንድ ሰው አፉ ላይ የመጠለትን ሁሉ መናገር የለበትም ካልን ደግሞ ከመናገሩ በፊት ምንድነው የምናገረው? መቼ ነው የምናገረው? እና የመሳሳሉትን ጥያቄዎች በመሳብ ዝግጅት እንዲያደርግ ግድ ይለዋል በማለት አብረርተውታል፡፡ ሌላ Bygate (1987:11) አንድ ሰው ንግግር ይችላል የሚባለው ከአንደበቱ ቅላፄና ምት ያለው የቃላት መውጣት በመቻሉ ሳይሆን ለተነሳበት ጉዳይ የሚውሉና ሀሳቡን በትክክል ሊያስተላልፉለት የሚችሉ ቃላት መምረጥ ሲችል ነው፡፡ ቃላትን በሚመርጥበት ጊዜ ይህ ቃል በዚህ ቃል ብናገረው አድማጭ ሊይዝልኝ ይችላል ወይ? የተነሳሁበትን አላማ ሳያደፈርስ አጥራቶ ሊያስተላልፍልኝ የሚችል ቃል ነው ወይ? የሚሉትን ማሰብ ይኖርበታል በማለት ገልፃዋል፡፡

ከምሁራኑ ማብራሪያ መረዳት እንደተቻለው የንግግር ክሂል ዳብሯል ማለት ሃሳብን በብቃት ለሌላው ለሁለተኛ አካል በትክክል ማስተላለፍ ሲቻል ነው፡፡ ብቃቱን ለመምጣት ደግሞ ሀሳብን በትክክል መደራጀት አሳማኝ ነጥቦችን የማፍለቅ፣ ተገቢ ቃላት መምረጥ እንዲሁም የንግግር ማበልፀጊያ ዘዴዎችን የመጠቀም ችሎታዎችን የሚጠይቅ ነው፡፡

## 2.2 የመናገር ክሂልን የማስተማር አላማ

ተማሪዎች የመናገር ክሂል በተግባር ሲማሩ ቃላዊ የተግባቦት ብቃታቸውን ያዳብራሉ፡፡ የተሻለ ማህበራዊ መስተጋብር መፍጠር ይችላሉ፤ አውድን መሠረት ያደረገ ንግግር የመጠቀም ልምዳቸውን ያሳድጋሉ፡፡ በመናገር ክሂል ትምህርት ጊዜ ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ ይህም በመናገር ክሂል ትምህርት የሚገኝ ጥቅም ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ የመናገር ክሂል ትምህርት ቃላዊ ተግባቦትን ለማዳበር ብቻም ሳይሆን ለሌሎች ክሂሎች መዳበርም አስተዋፅኦ

ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም የመናገር ክሂል ሲዳብር የማሳብ፣ የማዳመጥ፣ ማንባብና የመፃፍ ችሎታዎችም በተለያየ መንገድ ስለሚዳብሩ ነው፡፡ በመሆኑም የመናገር ክሂል ትምህርት የተማሪዎችን ሁለንታናዊ የቋንቋ ችሎታ በማዳበር ረገድ አይነተኛሚና የሚጫወት በመሆኑ አስፈላጊና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ክሂል ነው በማለት Nunan (2003, ማረው(2003) ገልፃዋል፡፡ ይህንንም ሀሳብ አስመልክተው በድሉ (2007፡87) በሀገራችን አብዛኞቹ ተማሪዎች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁት ጥሩ ንግግር ችሎታ ሳያዳብሩ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ከትምህርት ቤት በኂላ ባለው ህይወታቸው ያለምንም ችግር ሀሳባቸውን በንግግር ለመግለፅ ይቸገራሉ፡፡ በራስ ያለመተማመን (አይናፋርነት) መልዕክትን በምክንያትና ውጤት አቀናጅቶ ያለማቅረብና የቋንቋውን ስርዓት ያለመጠበቅ ከሚያገጥሟቸው ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

Harmer (2007:123) መናገር የሚናስተምርባቸውን እና ተማሪዎችም በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ የምንፈልግበት ሦስት ምክንያቶችን ጠቅሷዋል፡፡

- የመናገር ክሂል ተግባራት የልምምድ ዕድሎችን ማለትም ለዕውኑ አለም ንግግር የሚያገለግል የልምምድ ዕድል በክፍል ውስጥ ስለሚሰጡ፣
- ተማሪዎች የሚገለገሉባቸው የመናገር ክሂል ተግባራት ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ሁሉም ጥሩ እንዲሰሩ፣
- ተማሪዎች በአእምሯአቸው ያከማቹትን የቋንቋ ቅርፆችን የመገልገል ችሎታቸው ይጨምራል፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የመናገር ክሂልን በምናስተምርበት አላማ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ብቃት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ሲሆን ተማሪዎች ክፍል ውስጥ በሚያከናወኗቸው ተግባራት አማካይነት ትክክለኛነትንና የቋንቋ ፍላጎትን ወደ ሚፈለገው ደረጃ ለማድረስ ነው፡፡

## 2.3 የመናገር ክሂልን የመማር አስፈላጊነት

የመናገር ክሂልን ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ማስተማር ተማሪዎች ሀሳባቸውን ያለምንም መደናገር ንግግርን ማስተላለፍ እንዲችሉ የሚያደርጋቸውን ዕውቀትና ክሂሎት እንዲጨብጡ ለማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች ሳይፈሩ እና ሳያፍሩ በክፍል ውስጥ በጓደኞቻቸውና በመምህራኖቻቸው ፊት ሀሳባቸውን በትክክል መግለፅ የሚያስችላቸውን ችሎታ

አግኝተው በማህበራዊ ህይወታቸው የሚፈልጉትን ጉዳይ በንግግር ማስተላለፍ እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡ እንደ በድሉ (2007፡87) የንግግር ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት በተመለከተ እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በኋላ ያለ ህይወታቸው ያለምንም ችግር ሀሳባቸውን በንግግር ለመግለፅ ይቸገራሉ፡፡ እነዚህ ንዑሳን ክሂሎት በማዳበር ተማሪዎች ጥሩ የመናገር ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡

## 2.4 የመናገር ክሂል ተግባራት (activities) ባህርያት

ንግግር ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚከናወን ተግባቦታዊ ሂደት ነው፡፡ በንግግሩ ሂደትም ተናጋሪና አድማጭ ይሳተፋሉ፡፡ ስለሆነም ተግባራቱ ተማሪዎችን በጥንድ፣ በሶስትዮሽና በቡድን የሚያሳትፉና በራስ የመተማመን ስሜት በማዳበር ሀባቸውን እንዲገልፁ የሚያግዙ ሊሆኑ ይገባል፡፡ Ur (1996:128) በመጠቆም ተከታዮቹን የስኬታማ የመናገር ክሂል ተግባራት ባህሪያት ጠቅሰዋል፡፡

1. **ሁሉን ያማከለ ተሳትፎ፡-** የክፍል ውስጥ ክንውን ጥቂት ቁጥር ባላቸው ተማሪዎች ተፅዕኖ ስር ብቻ መውደቅ የለበትም፡፡ ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች የመናገር ዕድል ሊሰጣቸውና ተሳትፎኣቸው የተመጣጠነ ሊሆን ይገባል፡፡
2. **ብዙን ጊዜ ተማሪዎች እንዲናገሩ ማድረግ፡-** በተቻለ መጠን ለንግግር ተግባር የተሰጠውን ጊዜ በተማሪዎች ንግግር መሸፈን ይኖርበታል፤ ጉዳዩ ግልፅ ሆኖ እያለ ግን የክፍል ውስጥ ክንውን አብዛኛውን ጊዜ በመምህሩ ይሸፈናል፡፡ ስለዚህ የመምህሩን ሚና በመቀነስ የተማሪዎች መስተጋብራዊ ግንኙነት ጉልቶ እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
3. **ከፍተኛ ተነሳሽነት፡-** ተማሪዎች ለመናገር የሚነሳሱት በተመረጠው ርዕስ-ጉዳይ ከፍተኛ ፍላጐት ስለሚኖራቸውና ርዕሳ-ጉዳዩ የሚናገሩት አዲስ ሀሳብ ስለሚጭርባቸው ነው፡፡ ወይም ደግሞ በሂደቱ ተሳትፎ በማድረግ ለንግግር ተግባር አላማ መሳካት አስተዋፅኦ ለማበርከት ነው፡፡ ስለዚህ ተግባራቱ የተማሪዎቹን ተነሳሽነት የሚያሳድጉ ሊሆኑ ይገባል፡፡

   በአጠቃላይ መምህራን ከላይ የተጠቀሱትን የስኬታማ የንግግር ክሂል ባህሪያትን በቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ ክንውን ወቅት መተግበር ከቻሉ ተማሪዎች የመናገር ክሂልን በቀላሉ ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡

## 2.5 የንግግር ክሂል ትምህርት የማስተማር ደረጃዎች

ስለ ንግግር ክሂል ደረጃዎች ማሪው (1998) እና በድሉ (2007፡92) ጥሩ ንግግር ቅድመ ዝግጅትን እንደሚጠይቅ ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ ንግግር በሚቀርብበት ጊዜና ከንግግሩም በኋላ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ተግባራት አሉ፡፡ እነሱም የቅድመ ንግግር፣ የንግግር ጊዜና የድህረ ንግግር ተግባራት ተብለው በሦስት ይመደባሉ፡፡

### 2.5.1 ቅድመ ንግግር ተግባራት፡-

ቅድመ ንግግር ተግባራት ተማሪዎችና መምህራን የንግግር ትምህርትን በተግባር ከመጀመራቸው አስቀድመው ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ርዕስ መምረጥና መወሰን፣ ይህ ቅድመ ንግግር ተግባራት ተማሪዎች ንግግር ከማድረጋቸው አስቀድመው ንግግር የሚያዳርጉበትን ተስማሚ ወቅትና ለተማሪዎች አቅምና ደረጃ የሚመጥን በተያዘለት ሰዓት ውስጥ ሊጠናቀቅ የሚችል አንድ ነጠላ ጭብጥ የያዘ አጭርና ጠባብ ርዕስ የሚመረጥበት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ቅድመ ንግግር ተግባር ለክፍል ትምህርት የተመደበውን ሰዓት በአግባቡ ለመጠቀምና በሰዓቱ ለማጠናቀቅ እንዲሁም የዕለቱን ተግባር በአግባቡ ለመተግበር ያስችላል በማለት (በድሉ፣2007፡92)ገልፃዋል፡፡

በአጠቃላይ ንግግር የሚደረግበትን አስቀድመው መወሰንና ማንባብ በተቻለ መጠን ማስተላለፍ የሚፈለገውን ሀሳብ ለአድማጭ ሳይንዛዛ ግልፅ በሆነ መንገድ ለማቅረብ አጭርና ግልፅ የሆነ ሃሳብን የማቅረቢያ ሰዓትን በአግባቡ የመጠቀም ልምድን እንዲሁም በአጭር ጊዜ ውስጥ ዋና እና አስፈላጊ ሃሳቦችን ብቻ መርጦ የማቅረብ ብቃትን ይጨምራል፡፡

### 2.5.2 የንግግር ጊዜ ተግባራት፡-

ተማሪዎች ቅድመ ንግግር ተግባራት ካጠናቀቁ በኋላ በንግግር ተግባር ሲገቡ በንግግሩ መጀመሪያ ርዕሱን ለአድማጭ በሚገባ ማስተዋወቅ፣ የንግግሩን አላማ ባጭሩ ማስተዋወቅ፣ የአድማጭን ስሜትና ፍላጐት መጠበቅ፣ አድማጭን በአይን መቃኘት፣ ይስሙኝ ልንገራችሁ አይነት አቀራረብን በማስወገድ የአድማጮቹን ምላሽ መቀበል፣ መርጃ መሣሪያ ከስፈለገን ሳቢ አድርጐ ማቅረብ ከአድማጭ የሚመጡ ጥያቄዎችን በቅደም ተከተል በማስታወሻ መያዝ፡፡ በማለት በድሉ (2007፡ 93) ገልፃዋል፡፡

### 2.5.3 የድህረ ንግግር ተግባራት፡-

የድህረ ንግግር ተግባር አንድ ንግግር ከአበቃ በኋላ በሚከናወን ተግባር ሲሆን ተናጋሪዎች አድማጮቻቸው መልዕክቱን ምን ያህል እንደተረዱና የሚገመግሙበት ነው፡፡ ይህ የተወሰኑትን አድማጮች በዘፈቀደ በመምረጥ ንግግሩን ፍሬ ሃሳብ አስመልክቶ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ በማድረግ ወይም አጭር መጠይቅ ማዘጋጀት መጠይቁን በአድማጮች ማስሞላት በሚገኝ መረጃ በዕለቱ መተላለፍ የሚገባው መልዕክት በአግባቡ መተላለፉን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ይህም ያለፈውን የንግግር ሂደት በመገምገም በቀጣይ ለሚደረግ ንግግር የተሻለ ዝግጅት አድርጐ ሀሳብን በሚገባ ለማስተላለፍ ይረዳል፡፡ ስለዚህ ይህ ተግባር ንግግር አድራጊዎች ንግግራቸው ግቡን መምታቱንና አለመምታቱን በመገምገም የመናገር ብቃታቸውን ማሳደግ የሚችሉበት ስልት ነው በማለት በድሉ፣ (2007፡93)ገልፃዋል፡፡

በአጠቃላይ ንግግር አድራጊው አካል ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ንግግሩን በመረጃ አስደግፎ አጠር አድርጐ በማቅረብ አድማጭን ለማሳመን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ንግግር በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ግንዛቤ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

## 2.6 የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት

የመናገር ክሂልን ለማስተማር የተለያዩ ስልቶች በመኖራቸው የትምህርቱን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ስለሆኑ በተማሪዎቹና በሚቀርበው ተግባራት መካከል የሚኖረውን ሁኔታ በመረዳት አመቺ የሆነውን በመምረጥ ተጠቅሞ ማስተማር አስፈላጊ ነው፡፡ Harmer (2007:55) እንደሚሉት ጥሩ የመናገር ክሂል ተግባራት ሲዘጋጅ ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ በትምህርቱ እንዲሳተፉ ዕድል የሚሰጡና ከልምምድ በኋላ የመምህሩ ምጋቤ ምላሽ ግምት ውስጥ የሚያስገቡ ከሆኑ ተማሪዎች በትምህርታቸው እርካታ ያገኙሉ፡፡ ይህም ተማሪዎች የታለመው አላማ በቀላሉ እንዲደርሱበት ይረዳል፡፡ ተግባራቱ ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፉ ከሆነ ክፍሉ ያለምንም ችግር ተግባቦቱ የሰመረ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜት ከፍ በማድረግ በንግግር ሀሳብን የመግለፅ የቋንቋ ትምህርት ክፍል ባህል እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

የመናገር ክሂልን እንደክሂል ተማሪዎች እንዲያዳብሩት የሚረዱት ተግባራት በተለያዩ ምሁራን ስራዎች ውስጥ የተጠቀሱ ሲሆን Harmer (2007:129) ሲገልጹ የመረጃ ክፍተት ተግባራት አቅጣጫን ማሳየት፣ ነገሮችን (የስዕሎችን) ልዩነት መግለፅ፣ በሰንጠረዥ መልክ የቀረቡ መረጃዎችን ማሟላት ላይ ስለሚመሰረቱ ተግባራቱ የውስብስብነት ባህሪይ አይታይባቸውም፡፡

ይህም ባህሪያቸው ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቀላሉ እንዲገልጹ ይረዳቸዋል፡፡ ተረታ ተረቶች (ታሪኮች) ደግሞም የልጆችን ባህሪይ ከመቅረፅ በሻገር የልጆችን ስሜት የማነሳሳት ኃይላቸው ከፍተኛ ስለሆነ በዝቅተኛ ክፍሎች መጠቀሙ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ መምህራን ከላይ የተጠቀሱትን የስኬታማ የንግግር ክሂል ባህሪያት በቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ ክንውን ወቅት መተግበር ከቻሉ ተማሪዎች የመናገር ክሂልን በቀላሉ ሊዳብሩ ይችላሉ፡፡

## ሀ) ሚና ጨዋታ

ሚና ጨዋታ የሚለው ፅንሳ ሀሳብ ማንኛውንም እንቅስቃሴ የሚመለከት ሲሆን ተማሪዎች ስለ አንድ ትምህርት ርዕስ በተጨባጭ ዓላማ ላይ ያሉ ድርጊቶችን ወደ ክፍል ውስጥ በማምጣት ንግግርን የማስተማሪያ መንገድ ሲሆን በአቀራረቡ ድራማዊ ይዘት ያለው ምልልስ በመሆኑ ጥልቅ የሆነ ቁጥጥር እና ተግባራቱን በሚገባ በማጥናት የሚቀርብ ስለሆነ የንግግር ክሂልን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል(Byrne 1987, Nunan 1989) እንደ Richard እና Radgers (1989:79) ገለፃ "የመናገርን ክሂል ለማዳበር ይረዳ ዘንድ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ተማሪዎችን ለጭውውት የሚገብዙ፣ ሊያወያዩና ሊያከራክሩ የሚችሉ ሀሳብ እንዲሰጡ የሚያበረታቱ ተግባራት መኖር አለባቸው" በማለት ያስረዳሉ፡፡

መምህራን ሚናን ከተለያዩ ተግባራት ማለትም ከቀላል ምልልስ እስከ ውስብስብ ውክልና ከተለያዩ ደረጃዎች ጋር በማያያዝ መተግበር ይችላሉ፡፡ አንድን ሚና ወስዶ ተግባራዊ ማድረግ ለቋንቋ ንግግር ለዛ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ይህ ተግባር በጥንድ ወይም በቡድኖች በሚከናወን የተሻለ ውጤት ይታይበታል፡፡ ይህም የብዙ ተማሪዎች ተሳትፎ እንዲኖር ያበረታታል፡፡ የሚና ተግባራት በእውነተኛ ህይወት ላይ የተመሰረተ ሁኔታ ከሆነ ልምምዱ በጣም ጠቃሚ ነው አንዳንድ ተማሪዎች ሚናን መጫወት ለነፃ ውይይት ቀላል ሆኖ ያገኙታል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የዕውቀት እንቅፋት ስለማይገጥምባቸው አንዳንድ ተማሪዎች ሌላውን ሰው መስለው ሲጫወቱ ይደሰታሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የተለያዩ ሚናዎችን በፕሮግራም ሲጫወቱ ቋንቋቸውን በተጎዳኝ ይለማመዳሉ፤ ያሻሽላሉ በማለት Tricia Hedge (1996:278-280) ጠቅሰዋል፡፡

## ለ) ክርክር

በአንድ ጉዳይ ላይ የግል አቋምን እንደመንፀባረቂያ ይዞት በመሆኑ ገለፀው የንግግር ክሂል አዳባሪነቱ አጠያያቂ አይሆንም፡፡ በዚህ የንግግር መለማመጃ አሁንም ለውጤታማነቱ መምህሩ የጎላ ሚና አለው፡፡ ክርክርም ሆነ ውይይት ሲካሄድ የማዳመጥ ክሂልም ይዳብራል፡፡ የመናገር ክሂልን በማስተማር ሲተሳብ የተለያዩ የሥነፅሁፍ ስራዎችን ወደ ክፍል አምጥቶ በማስነበብ በስነፅሁፍ ስራው ውስጥ ያሉ ገፀ-ባህሪያት ወደ ግጭት ከገቡ በኋላ ከግጭት ለመውጣት የሚጠቀሙበትን የተለያየ መንገድ መነሻ በማድረግ ፍላጎታቸውን መሠረት ያደረገ ምደባ በማድረግ ተማሪዎችን በቡድን በመመደብ የሚደግፉትን ከግጭት የማውጫ መንገድ ደግፈው እንዲከረከሩና ምክንያታዊ የመከራከሪያ ሀሳብ እንዲያቀርቡ በማድረግ ንግግርን ማስተማር የተሻለ ለውጥ ያመጣል  በማለት (በድሉ 2007)ገልፃዋል፡፡

በሌላ በኩል በክርክር ጊዜ ለመከራከሪያነት የሚመረጡ ርዕሶች (ሃሳቦች) ተመጣጣኝ ባህርይ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ባህሪያቸው ተመጣጣኝ ካልሆኑ ግን ተከራካሪዎች አስቀድመው የማሸነፍ ወይም የመሸነፍ ስሜት ስለሚሰማቸው ክርክራቸው የሞቀና ከፍተኛ ፉክክር የሚታይበት አይሆንም፡፡ ይህም በተማሪዎች የመናገር ክሂል ላይ አወንታዊ ለውጥ ሊያመጣ አይችልም፡፡ በመሆኑም ለመከራከሪያነት የሚመረጡ ርዕስ ጉዳዮች ተመጣጣኝ መሆን ይኖርባቸዋል ሲሉ (ጌታቸው 2004) ገልፃዋል፡፡

## ሐ) ውይይት

የቡድን ውይይት ተማሪዎችን አንድ የጋራ የሆነ ድምዳሜ ላይ ለማድረስ የሚያስችል የፊት ለፊት ሀሳብ ልውውጥ የንግግር ዘዴ በመሆኑ የጋራ የሆነ አላማ ለማሳካት በተወሰኑ ሰዎች መካከል የሚካሄድ እንደሆነ Byriacou (1998: 77) ይገልፃሉ፡፡

Lang and Pater (1985: 209) የቡድን ውይይት በተመለከተ ሲያብራሩ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ብቃት የሚያሳድግ ነው፡፡ ምክንያቱም በተመሳሳይ ወቅት የሚያሳትፈው ብዙዎችን እንደሆነ ጭምር ገልፃዋል፡፡

ከመምህራን የሚጠበቀው ውይይትን ለንግግር ክሂል ማስተማርያነት እንዴት መቅረብ እንደሚገባቸው ማወቅ ነው፡፡ ስለዚህ ዋናው ጉዳይ መሆን የለበትም ተብሎ የሚቀርበው ርዕስ የተማሪዎቹን ዕድሜ፣ አካባቢ፣ የትምህርት ደረጃ ወዘተ… ጋር መጣጣም ተግባራቱን መጠቀም እንደሚቻል መምህራን በውል ሊገነዘቡት ይገባል፡፡ እንዲሁም አንድን ተማሪ ሳያስባው በክፍል

ጓደኞቹ ፊት ቀርበው ተናገር ከማለት የዝግጅት ጊዜ አስፈላጊ መሆኑን መጤን ያሻል፡፡ ይህንኑ በመጠናከር (Tericia Hedge 1996:277) መምህራን ብዙን ጊዜ በቡድን ያልተዋቀሩ የንግግር ብቃትን የሚያሻሽሉ ተግባራት ያስጨንቃቸዋል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በተግባራቱ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ሊቸገሩ ይችላሉ በማለት ገልፆዋል፡፡

በተጨማሪም ነፃ ውይይት የንግግር ለዛን ለማዳበር መልካም አጋጣሚዎችን መፍጠር ይችላል፡፡ በተለያዩ ጊዜ በነፃ ውይይት ተማሪዎች እንዲሳተፉ በማድረግ በርካታ ርዕስ ላይ ለምሳሌ በፍላጎታቸው፣ ሀሳቦች፣ ታሪኮች እና ልምምዶቻቸው የንግግር ችሎታቸውን ሊያደብሩ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ቁሳቁሶችንም ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡ እዚህም ላይ ተማሪዎች የሚስማመባቸው እና የማይስማሙባቸውን ሀሳቦች፣ (ምርጫቸውን) እና ንፅፅር እንዲያደርጉ ዕድል ልሰጣቸው ይችላል፡፡ ከነፃ ውይይት በተጨማሪ ተማሪዎች ለምልልስ አስፈላጊ የሆነ Harmer(2007:129-130) ይህንኑ በማጠናከር የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ማለማመድ የሚችሉ ተግባራትን ሲገልፁ፡- ተማሪዎች የሚፈልጉትን ርዕስ በመምረጥ እርስ በርስ ቃለመጠይቅ እንዲደራረጉ ማድረግ፣ ተማሪዎች የተለያዩ መረጃዎችን ሰብስበው በማደራጀትና በመለማመድ በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ማድረግ ወይም በቤታቸው ያነበቡትን ቅንጫቢ ወይም ሙሉ ስራ በንግግር እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ ተማሪዎችን በቡድን በመመደብ ከሚደግፉት ሀሳብ አንፃር ወግነው እንዲከረከሩ ማድረግ፣ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማዳበር ጥሩ የክፍል ቋንቋ እንዲጠቀሙ ያበረታታል በሌለኛው ተናገሪ ላይ በተወሰነ ጊዜ ምስል እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ በርግጥም ነፃ ውይይት ከሌሎች ተግባራት የበላይነትን ይይዛል፡፡

ይኸውም ለተማሪዎች የርስ በርስ ግንኙነት አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡ ከላይ የተገለፁት ተግባራት አንድ አማርኛ ቋንቋ መምህር የመናገር ክሂል በክፍል ውስጥ ልተገብር ሲያስብ ሊያከናውናቸው የሚገቡ በመሆናቸው ከነዚህም ተግባራት በመጠቀም መምህሩ ተማሪዎቹን በሚገባ ማለማመድ ይጠበቅበታል፡፡

## መ) ታሪክ መናገር

Harmer (2007:129) ተማሪዎች ከዚህ በፊት የሰሟቸውን ታሪኮች ደግመው እንዲናገሩ ማድረግ፣ የየራሳቸውን ታሪኮች ፈጥረው እንዲናገሩ ማበረታታትና ስለዩኣቸው ወይም ስለአከናውኗቸው ነገሮች እንዲናገሩ ዕድል መስጠት ክፍል ውስጥ ንግግር ማለማመድ ይቻላል፡፡ ተማሪዎች በቡድን በቡድን ይቀመጣሉ፡፡ ለእያንዳንዱ ቡድን ተከታታይነት ያላቸውን መልዕክት አዛል ስዕሎች ይሰጣል፡፡ ቡዱኖች ስዕሎቹን ከተመለከቷቸው በኋላ ይሰበስባሉ ከዚያም

ከመጀመሪያዎቹ ቡዱኖች አንዳንድ አባል የያዙ ሌሎች አዳዲስ ቡዱኖች ይደራጃሉ፡፡ አዲሶቹ ቡዱኖች ቀደም ሲል ያዩት ስዕላዊ መግለጫ ምን መልዕክት እንደሚያስተላለፍ ይናገራሉ፡፡ በመጨረሻም እያንዳንዱ ቡድን ያቀረበው ታሪክ ተመሳሳይ ሀሳብ የያዘ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ቡዱኖች የየራሳቸውን ታሪክ ለክፍሉ ያቀርባሉ፡፡

Harmer (2007:130) እንደገለጹት "የተማሪዎችን የመተረክ ችሎታ ለማሳደግ የየራሳቸውን ሁኔታ ለምሳሌ በሰውነታቸው ላይ ስላለ ጠባሳ፣ ስለፀጉራቸው፣ ስለጌጦቻቸው፣ ስላዩት ትምህርት መሣሪያዎቻቸውና ስዕሎቻቸው ወይም ደግሞ ቀደም ሲል ስላሳለፉት በጎ ወይም መጥፎ ገጠመኝ ወዘተ... እንዲተርኩ የሚያነሳሱ ጥያቄዎችን መምህሩ እንደ መነሻ ቢጠቀም ውጤቱ በጣም የተሻለ ይሆናል" ይላል፡፡ Sesnan (1997:116) ከዚህ በፊት የሰሟቸውን ታሪኮች ደግመው እንዲናገሩ ማድረግ የየራሳቸውን ታሪኮች ፈጥረው እንደናገሩ ማበረታታት እና ስለአዩኣቸው ወይም ስለአከናውናቸው ነገሮች ለክፍሉ እንዲናገሩ ዕድል መስጠት የተማሪዎችን የመተረክ ችሎታ ለማሳደግ ይረዳል፡፡

ስለዚህ መምህራን በየቋንቋው በቃል በሚተረኩ ወይም በፅሁፍ የቀረቡ ታሪኮች የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ያላቸውን ፋይዳ ተገንዝበው ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ለሚያቀርቡት ንግግር ታሪኮችን በግብኣትነት እንዲገለገሉባቸው ማድረጉ የመናገር ክሂል አቀራረቡን ቀና እንደሚያደርገው በውል ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

## ሠ) ጨዋታዎች

Sesnan (1997:116) "ጨዋታዎች ደስታ እየፈጠሩ የልጆችን የቋንቋ ችሎታ ለማሻሻል ይረዳሉ" ይላሉ፡፡ ተማሪዎች በቡድን መደራጀት፣ ለጨዋታው ግልፅ ህግ ማዘጋጀት፣ የጨዋታው አሸናፊዎች እስከሚታወቁበት ጊዜ ድረስ ሂደቱ ሁሉንም የቡዱኑን አባላት የሚያሳትፍ መሆኑን ማወቅ፣ ተሸናፊዎች ከጨዋታው ውጭ ከሆኑ በኋላ እንደገና ወደ ጨዋታው የሚመለሱበት ህግ መኖሩን ማረጋገጥ፣ ወይም ጨዋታውን አሳጥሮ ቶሎ እንዲያልቅ ማድረግ ከጨዋታው በፊት የሚታሰብባቸው ጉዳዮች እንዲሆኑ አስገነዝበዋል፡፡ ስለዚህ ልጆች ጨዋታዎችን እተየጫወቱ እግረ መንገዳቸውን የቋንቋ ችሎታቸውን ማሳደግ ይችሉ ዘንድ የመለማመጃ ተግባራቱ እንዴት እንደሚከናወኑ ዝርዝር መረጃዎቹን መምህሩ በቅድሚያ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ የተለያዩ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል ውስጥ ጨዋታዎች ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡ ምክንያቱም የተወሰኑ ተማሪዎች ጨዋታውን ሲችሉ ሌሎች ደግሞ ጨዋታውን ፈፅሞ ሰምተው የማያውቁት ሊሆንባቸው ይችላል፡፡ ይህም የጨዋታዎች ውስንነት

መሆኑ ነው። ስለሆነም መምህሩ ጨዋታዎችን ክፍል ውስጥ ለመተግበር ሲያስብ የተማሪዎችን የዕድሜ፣ የባህልና የቅድመ እውቀታቸውን በመረዳት ችግሩን መፍታት ይጠበቅበታል።

## ረ) ቃላዊ ሪፖርት

ተማሪዎች ያነበቡትንና ያዳመጡትን ጉዳይ በራሳቸው የቃላት አጠቃቀምና አገላለፅ ችሎታ በንግግር የሚያቀርቡበት ነው። ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ቃላዊ ሪፖርት በሚያቀርቡበት ጊዜ አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር መምህራን ማከናወን ያለባቸው ተግባራት ይኖርባቸዋል። ከክፍለጊዜ አስቀድሞ ተማሪዎቹ በቂ ዝግጅት ማድረጋቸውን ማረጋገጥ፣ ለሪፖርቱ አስፈላጊ ሰዓቶችን ብቻ ማስታወሻ እንዲይዙና ሌለውን ጉዳይ በቃል ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ ሪፖርቱ ከቀረበ በኋላ አድማጮች ያልገባቸውን ጉዳይ እንድጠይቁ ማድረግ፣ አቅራቢው ለተጠየቁ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥ ማድረግ ወዘተ… ናቸው በማለት በድሉ (2007፡95) ዘርዝረዋል።

## ሰ) ችግሮችን አፍልቆ መፍትሔ መሻት

Bygate (1987:80) በዚህ ደረጃ ማንኛውመ የመናገር ዕድል ለተማሪዎች በመስጠት ቋንቋውን በራሳቸው እንዲጠቀሙበት (በነፃነት እንድገልፁ) ማድረግ ነው። በአፍልቆት ደረጃ ዋናው ትኩረት ተማሪዎች በቀላሉ እና በነፃነት የሚግባቡትን ዐውድ መፍጠር እንዲሁም በጋራ የሚሠሩ ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

የዚህ ተግባር ዋና አላማ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ችግሮች ከመፍታት ባለፈ ሳይታወቀቸው እርስ በርስ በሚያደርጉት ተረክቦ የመናገር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ሲሆን ለመለማመጃ የሚቀርቡት ተግባራትም ለመሥራት የተማሪዎችን ችሎታ መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ከላይ የቀረበውን ተግባር ለማከናወን ሦስት ደረጃዎችን መከተል አስፈላጊ እንደሆነ Bygate (1987:81) ይጠቅሳሉ። የመጀመሪያው አስፈላጊውን መረጃ የመስጫ ጊዜ ሲሆን ሁለተኛ ችግሩን ለመፍታት የሚከናወን ውይይት ነው። የመጨረሻው ደረጃ ደግሞ የመምህሩ ክትትል ነው።

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው እንደነዚህ አይነት መለማመጃዎች የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ከማዳበራቸውም በላይ የተማሪዎችን ችግር ፈቺነት አቅም ለማሳደግ ያላቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። ስለዚህ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ የክፍል ደረጃውን ያገነዘቡ መልመጃዎችን መርጦ በመስጠት ተማሪዎች እንዲለማመዱ ማድረግ ከመምህራን ይጠበቃል።

## 2.7 የመናገር ክሂል ሲተገበር የሚያጋጥሙ ችግሮች

ንግግር ተማሪዎች ክፍል ውስጥ በሚማሩበት ጊዜ የሚያገጥሙ እንቅፋቶች በቋንቋ ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት በሚከናወንበት ወቅት ተግባሩን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ሁኔታዎች ከመምህሩም፣ ከተማሪዎችም፣ ከመማሪያ ክፍል ሁኔታ እና ከመማሪያ መፅሐፍት ጋር የሚያያዙ ችግሮች በመሆናቸው መፍትሔ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ከመምህሩ አኳያ የዝግጅት ማነስ፣ የክፍል አመራር ችሎታ መጣት ወዘተ… ሲጠቀስ ከተማሪ አኳያ መታቀብ፣ የሚናገሩት ነገር መጣት፣ ዝቅተኛ ወይም ሁሉን ያለማከለ ተሳትፎ አለማከናወን ናቸው በማለት Ur (1996:121) ገልፀዋል፡፡ ከተጠቀሱት ችግሮች ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት የሚከሰቱ ችግሮች ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት የሚከሰቱ ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ሀ) መታቀብ፡-** ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ የፍርሀት ስሜት ያድርባቸዋል፤ በነፃነት ከመናገር ይቆጣባሉ፣ ብንሳሳትስ የሚል የተሳሳተ አመለካከት ስለሚይዙ በጓደኞቻቸውና በመምህሩ ፊት ከመናገር ይቆጣባሉ፡፡ በተጨማሪም ትችትን በመፍራትና ንግግራችን የሌሎችን ስሜት መሳብ አይችልም በሚል እምነት ሀሳባቸውን በውስጣቸው አምቀው የመያዝ ባህርይ ይታይባቸዋል፡፡ በዚህ የተነሳ በክፍል ውስጥ ለንግግር በሚዘጋጁ ተግባራት በፈቃደኝነት አይሳተፉም፡፡

**ለ) የሚነገሩት ነገር መጣት፡-** ተማሪዎች የመናገር ፍላጐት እያላቸው አንዳንድ ጊዜ ለንግግር ስለተመረጠው ጉዳይ በቂ መረጃ ስለማይኖረቸው ለመናገር አይደፍሩም፡፡ ተማሪዎች ለንግግር በተመረጠው ርዕስ-ጉዳይ ዙሪያ በቂ ዳራዊ ዕውቀት ከሌላቸው (የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ፣ ፍላጎት ያለገናዘበ ከሆነ) ለመናገር ግላዊ ፍላጐትና ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፤ ይህ አይነቱ ሁኔታ በተደጋጋሚ ከተከሰተ ተማሪዎች ለንግግር ስር የሰደደ ጥላቻ ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡

**ሐ) ዝቅተኛ ወይም ሁሉን ያለማከለ ተሳትፎ፡-** አብዛኛውን ጊዜ በክፍል ውስጥ በንግግር ተግባራት በአንድ ጊዜ የሚሳተፉት አንድ ተማሪ ብቻ ነው፡፡ በዚህ አይነቱ ሁኔታ በርካታ ተማሪዎች በንግግር ተግባር ላይ ለማሳተፍ ለቋንቋ ትምህርት ከተመደበው ጊዜ ጋር ሊጣጣም የማይችል ተግባር ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የተወሰኑ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባርን በመቆጣጠር የሌሎች ተሳትፎ ውስን እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

## 2.8 የመናገር ክሂል ሲተገበር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማስወገድ የሚጠቅሙ ተግባራት

Ur(1996:121) እና ቅማዩኮ(2006:28-29) ንግግርን በማስተማር ሂደት ለሚያጋጥሙ ችግሮች የሚከተሉትን ተግባራት በመፍትሔነት የጠቆሙ ሲሆን ተግባራቱ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

### 2.8.1 የቡድን ሥራ መጠቀም፡-

ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ንግግር ሲያደርጉ በቡድን ሦስት ወይም አራት ሆነው በርዕሱ ላይ የቻሉትን ያህል እንዲያስቡ ወይም ምን ምን ነጥቦች ሊነሱ እንደሚችሉ እንዲገምቱ በማድረግ ንግግር ማለማመድ ይቻላል፡፡ ተማሪዎች በዚህ ተግባር ማሳተፍ የሚያስገኝላቸው ጠቀሜታ በክፍሉ ፊት ባንድ ጊዜ ቆሞ ከመናገር ይልቅ ንግግርን በተግባር ማለማመድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በመሆኑም የመናገር ዕድል ስለሚያገኙ ንግግራቸውን የሚያዳብሩበት መልካም አጋጣሚ ያገኛሉ፡፡

### 2.8.2 ተግባሩን በቀላል ቋንቋ እንዲቀርብ ማድረግ፣

ተማሪዎች ሀሳባቸውን በራሳቸው የቃላት አጠቃቀምና የአገላለፅ ችሎታ ተጠቅመው እንዲያቀርቡ ማድረግ የንግግርን ተግባር ከባድ አድርገው እንዳያስቡት ያደርጋል፤ በራስ የመተማመን ደረጃቸው ከፍ ያደርጋል በማለት በድሉ (2007፡90) ገልፃዋል፡፡ ይህ አገላለፅ ተማሪዎች ከሌላ ጥገኝነት ነፃ ሆነው አንዳንድ ነገር በራሳቸው አገላለፅና የቃላት አጠቃቀም ለመግለፅ ስለሚያስችላቸው የንግግር ክሂላቸውን ለማጎልበት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

### 2.8.3 ፍላጎት ለማነሳሳት ሳቢና አነቃቂ የመወያየ ርዕስ ወይም ተግባር መምረጥ፡-

ተማሪዎችን ለንግግር የሚያነሳሳና ሊያነጋግር የሚችል ሳፊ ሀሳብ የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡ ርዕሱ የተመረጠው ወይም የተዘጋጀው የተማሪዎችን ፍላጐት መሠረት አድርጐ ከሆነ የተማሪዎች ተሳትፎ ይጨምራል፡፡ ስለዚህ የመናገር ክሂልን የክፍል ውስጥ ክንውን ውጤታማ ለማድረግ በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተረክቦ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ችግሮችን ለመቀነስ በመፍትሔነት የቀረቡትን ነጥቦች ተግባራዊ ለማድረግ አለ የማይባል ጉዳይ መሆኑን መምህራን ሊገነዘቡት ይገባል በማለት በድሉ 2007፡90 አብራርተዋል፡፡ በተጨማሪም የሚመረጠው ርዕስ በተማሪው የህይወት ገጠመኝ ዙሪያ ቢሆን ይመረጣል፡፡

## 2.9 በመናገር ክሂል ትምህርት ጊዜ የመምህሩ ሚና

Nunan (1991:87) "አንድ መምህር በተግባቦታዊ የቋንቋ ክሂል ውስጥ ሦስት ዋና ዋና ሚናዎች እንዳሉት ጠቅሰዋል፡፡ የመጀመሪያው በተግባቦታዊ ሂደት አመቻች መሆን፣ ሁለተኛ ሚናው ደግሞ ተሳታፊነት ሲሆን፣ ሦስተኛው ተግባሩ የመማር ሂደቱን መከታተል ነው" ይላሉ፡፡ አንድ የቋንቋ መምህር በቡድን ሥራ ወቅት ተማሪዎች ሌሎች የቡድኑ አባላት ስለሚሰነዝሩት ሀሳብ ከበሬታ መስጠት እንዳለባቸው መምከር የቡድን አባላት ስህተት አንዱ የመማሪያ መንገድ መሆኑን እንዲገነዘቡ ማድረግና ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች ነፃ ሆነው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ማበረታታት፣ የመረጃ ምንጭ በመሆን የክፍሉን መስተጋብራዊ ግንኙነት ከፍ በማድረግ የተማሪዎች የንግግር ችሎታ እንዲጐለብት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

ተማሪዎች በራሳቸው ግላዊ ፍላጐትና በተለያየ ፅንሳ ሀሳቦች ዙሪያ የርስ በርስ ውይይት እንዲያደርጉ ማበረታታት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚቀርቡ ልዩ ልዩ ማለማመጃ ተግባራት በንቃትና በትጋት እንዲሳተፉ ማጠናከር ማበረታታት፣ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችም አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት እንዲሳተፉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተማሪዎች ተግባራዊ የሚደረጉ የመወያየና የመከራከሪያ ርዕሶችን ራሳቸው ተማሪዎች የሚመርጡበትን ዕድል መስጠትና በመረጡት ርዕስ እንዲከረከሩና እንዲወያዩ ማድረግ፣ ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያት የሰው ፊት በመፍራት፣ በቸልተኝነት መግለፅ የሚፈልጉትን ጉዳይ ከመግለፅ ወደኋላ እንዳይሉ ማበረታታትና ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ የመናገር ክሂል በአንድ ጊዜ ሳይሆን ተከታታይነት ያለው ልምምድ እንዲያደርጉ አቅጣጫ በማሳየት ወዘተ… መበደኛ የሆነ የመናገር ብቃታቸውን እንዲያዳብሩና ንግግራቸውን መደበኛ ወደሆነው የቋንቋ

አጠቃቀም ሥርዓት እንዲያሳድጉ ጥረት የማድረግ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል በማለት (በድሉ 2007፣ ጌታቸው 2004) ገልፀዋል ፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ባሉበት ሁኔታ የመናገር ክሂልን ማስተማር ምን ያህል ከባድ እንደሆነ መረዳት አያስቸግርም፡፡ ስለዚህ መምህራን ችግሮችን በወጉ ለይተው በመረዳት የተለያዩ ቴክኒኮችንና ያሠራር ሥርዓቶችን ማመቻቸት ጠቀሚ እንደሆነ መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.10 በመናገር ክሂል ትምህርት ጊዜ የተማሪው ሚና

የመናገር ክሂል ትምህርት ትግበራን የሚጠይቅ በመሆኑ ለተማሪዎች የመናገር ክሂል መዳበርም ሆነ አለመዳበር መምህራን ብቸኛ ምክንያቶች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ንግግር በልምምድ የሚዳብር በመሆኑና ተማሪዎች ለመናገር ክሂል ብቃታቸው መዳበር የመጀመሪያዎቹ ባለድርሻ አካላት በመሆናቸው ነው በማለት (Bygate 1987) ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ ተማሪዎች ለክሂሉ መዳበር የነሱ ድርሻና ኃላፊነት ትልቅ ዋጋ ያለው መሆኑን በመገንዘብ ከመምህራን ጥገኝነት ተላቀው የራሳቸውን ጥረትና ተግባራዊ ልምምድ በማድረግ፣ ሌሎችን በማገዝና በመርዳት የነሱንና የሌሎችን ተማሪዎች የመናገር ብቃት ለማሳደግ ኃላፊነታቸውንና የማይተካ ሚናቸውን መወጣት የሚጠበቅባቸው መሆኑን ከላይ ከቀረበው ሃሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም መምህራንና ተማሪዎች የየራሳቸውን ሚና በአግባቡ ከተወጡ በተማሪዎች የመናገር ብቃት ላይ አዎንታዊ ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡

## 2.11 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት አጥኚ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ቀደምት ጥናቶች በማየት ባደረገው ፍተሻ ሁለት የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፎችን አግኝቷል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸው 1ኛ አብርሃም ገ/ዮሐንስ “በ 2003) በአፋር ክልል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን የማስተማር ዘዴ” በሚል የተደረገ ጥናት ነው፡፡ 2ኛ መዝገባ ገ/ሚካኤል “የአማርኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበር በ10ኛ ክፍል ከመቐለ ከተማ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች (በ2008 ዓ.ም) ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ የተደረገ ጥናት ነው፡፡ አብርሃም ገ/ዮሐንስ ይህ ጥናት ትኩረት የአማርኛ ቋንቋ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ሃሳባቸውን በንግግር የመግለፅ ችሎታቸውን ለማዳበር ይችሉ ዘንድ የተለያዩ ሥነ ዘዴዎችን ቢጠቀሙ ለንግግር ክሂል አተገባበር ለመለማመጃነት ሊያገለግሉ ቢችሉም በቋንቋ ተጠቅመው ሀሳባቸውን የመግለፅን ተግባቦት የመፍጠር ብቃት የሚያዳብሩ እንዳልሆኑ በግኝት ላይ አጥኚው ጠቅሷል፡፡

ሁለተኛ የጥናቱ አቅራቢ መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ አጋዥ መርጃ መሣሪያዎችን ያለመጠቀም፣ ተማሪዎች በቡድን ወይም በጥንድ በመሆን እርስ በርሳቸው ሀሳብ እንዲለዋወጡ፣ እንዲናገሩ፣ እንዲከራከሩ፣ እንዲወያዩ የማያደርጋቸው መሆናቸውን፣ ተማሪዎች ሀሳባቸውን የመግለፅ ችሎታ የሚያዳብሩ ወደ ዋናው የንግግር ተግባር ከመግባታቸው በፊት ተማሪዎቻቸውን የማያነቃቁ፣ በመፅሀፉ ውስጥ ያሉትን የንግግር መልመጃዎችን የማያሰሯቸው መሆናቸውን አጥኚው ጠቅሷል፡፡

ይህ ጥናት ከቀደሚዎች ጥናቶች ጋር አንድ የሚያደርገው ሁሉም አጥኚዎች የመናገር ክሂል ትምህርት መሠረት አድርገው መጠናታቸው እና በኢ-አፈ ፈት ተማሪዎች ላይ መተኮራቸው ሲሆን በአጠናን ስልቱ፣ በክፍል ደረጃ፣ በጥናቱ ቦታ፣ በጥናቱ ዘመን እና በተጠኚዎቹ ዳራ የተለየ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

በምዕራፍ አንድ ለመግለፅ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ትኩረት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አተገባባር ግምገማ ፍተሻ ነው፡፡ ጥናቱ የተከተለው ዓይነታዊ እና መጠናዊ ምርምር ዘዴ ሲሆን አቀራረቡ ገላጭ ነው፡፡

ከዚያም በመቀጠል የተሰበሰቡት መረጃዎች ለመተንተን ጥናቱን የተጠቀመባቸው መተንተኛ ስልቶች ተገልፆ የመረጃ መሰባሰቢያ አግባብነት እና አስተማማኝነት እንዴት እንደተፈተሻ መብራሪያ ቀርቧል፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ

**ሠንጠረዥ 1:- በጥናቱ የተካተቱ ትምህርት ቤቶች፣ የተማሪዎች እና የመምህራን ብዛት የናሙና መጠን እና የምልከታ ጊዜ መግለጫ**

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት | | የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን | | የምልከታው ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በትምህርት ቤት | ናሙና | በትምህርትር ቤት | የመጠይቅ ናሙና | |
| 1 | ዶንጋ ጡንጦ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 680 | 28 | 3 | 1 | 3 |
| 2 | አመለቃ ሁለተኛ ደረጃ ትምምህርት ቤት | 530 | 28 | 2 | 1 | 3 |
| 3 | ሶድቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 315 | 28 | 2 | 1 | 3 |
| 4 | ሙጉንጃ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 400 | 28 | 2 | 1 | 3 |

### 3.2.1.የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት በደቡብ ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን በሀደሮ ጡንጦ ወረዳ ስር ከሚገኙ ከመንግሥት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በዶንጋ ጡንጦ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በአመለቃ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በሶድቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በመጉንጃ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተካሄደዋል፡፡ እነዚህን ትምህርት ቤቶች አጥኚው በአመቺ ናሙና መርጧዋል፡፡ የተመረጡበትም ምክንያት በሥራ ላይ በመሆን የሚከናወነው ምርምር በመሆኑ ከሚሰራበት ትምህርት ቤት ጋር ቅርበት ስላለቸው እና ከሌሎች ትምህርት ቤቶች ይልቅ ለጥናቱ ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት ጊዜና ጉልበትን ከመቆጠብ በተጨማሪ ጥናቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ያደርገዋል ተብሎ ስለታሰበበት ነው፡፡

### 3.2.2.የመመሪያ ክፍል ናሙና አመራረጥ

የመማሪያ ክፍሎች አመራረጥ በተመለከተ ተተኳሪ መምህራን ከሚገቡባቸው ክፍሎች ውስጥ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤቶች አንዳንድ ምድብ በድምሩ አራት ምድቦች በዕጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

### 3.2.3.የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በተመረጡት አራት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥራቸው ዘጠኝ ሲሆን አራቱ የጥናቱ ተተኳሪ ሆነው ተመርጠዋል፡፡ አመራረጡም በኢላማዊ ናሙና አማካኝነት ሲሆን ለጥናቱ ጠቃሚ የሆነ መረጃ ያስገኛሉ ተብለው የታሰቡት መምህራን በናሙናነት ተጠኚ እንዲሆኑ ተመርጠዋል፡፡ ከየትምህርት ቤቱ አንድ አንድ ተጠኚ መምህራን ብቻ በጥናቱ እንዲታቀፉ ተደርገዋል፡፡

### 3.2.4.የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በተመረጠው የክፍል ደረጃ የተመረጡት መምህራን ከሚያስተምሩባቸው ክፍሎች መካከል የተመረጡት ተማሪዎች በቀላል የዕጣ ናሙና ዘዴ አራቱ ክፍሎች ተመርጠዋል፡፡ ተማሪዎች እኩል ዕድል በሚሰጠው ናሙና ዘዴ ተመርጠው በጥናቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ ተማሪዎች እኩል ዕድል በሚሰጠው በቀላል የዕጣ ናሙና የተመረጡበት ምክንያት እያንዳንዱ የጥናቱ አካላይ አባል ናሙና ሆኖ ለመመረጥ እኩል ዕድል ስላለው ከሌሎች የናሙና መምረጫ ስልቶች ይልቅ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የመመረጥ ዕድል ስለሚሰጥ ነው፡፡

## 3.3. መረጃ መሰባሰቢያ ዘዴዎች

የአንድ ጥናት ውጤት አስተማማኝነትንና ትክክለኛነትን ከፍ ለማድረግ የተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ መረጃዎች ለማሰብሰብ ጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 3.3.1.የክፍል ውስጥ ምልከታ

በቋንቋ ትምህርት ተግባቦታዊ ክፍል ውስጥ መምህሩም ሆነ ተማሪዎች የየራሳቸው የሆነ ሚና አላቸው፡፡ ለዚህ ጥናት ዋና የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የክፍል ውስጥ አተገባበር በመሆኑ የመምህራኑ የመናገር ክሂል አተገባባር ምን እንደሚመስል ለመቃኘት ስለሚያስችል ነው፡፡ ከምልከታው የሚገኙ መረጃዎች ለጥናቱ በተመረጠው ትምህርት ቤቶች የሚስተዋለውን የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል መማር ማስተማር ክንውን በቀጥታ ማየት ስለሚቻል ተጨባጭ ስለሚሆኑ ነው፡፡ ምልከታውም የተካሄደው የተደራጀ የምልከታ ቅፅ በቅድሚያ በማዘጋጀት ነው፡፡ የመናገር ክሂል ክፍል ውስጥ እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉለት ለመመርመር ሲሆን ምልከታው የተደረገው በአራት ዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ በመታዘብ ነው፡፡ ምልከታው በእያንዳንዱ ተጠኚ መምህራን ላይ ሶስት ሶስት ጊዜ ተካሄዷል፡፡

### 3.3.2.የፅሁፍ መጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቅ ከሌሎች መሰብሰቢያ ዘዴዎች ሲነፃፃር ጊዜን፣ ጉልበትንና ገንዘብን ቆጣቢ በመሆኑ፣ የመለሾችን ማንነት ስለማይገልፅ መላሾች አስተማማኝ መረጃ እንዲሰጡ በማበረታታትና ለሁሉም ተጠኚዎች አንድ አይነት ጥያቄ በማቅረቡ በምርምር መስኮች የበለጠ ጥቅም ላይ እንደሚውል ያለው እንዳወቀ (2009፡152) ጠቅሰዋል፡፡ የፅሁፍ መጠይቅ መሠረታዊ አላማው በተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ ያልተገኙ መረጃዎችን ለመሰብሰብና በሌሎች መረጃ ምንጮች የተገኘውን መረጃ በበለጠ ለማዳበር ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ስለሚያግዝ ነው፡፡ የፅሁፍ መጠይቅ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ለተመሳሳይ አላማ ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው፡፡ ለመምህራን የተዘጋጀ የፅሁፍ መጠይቅ ለተተኳሪዎቹ መምህራን ተበትኖ በቂ ጊዜ አገኝተው እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ለተማሪዎች የተዘጋጀው የፅሁፍ መጠይቅም አጥኚው በየትምህርት ቤቶቹ በመገኘት የተመረጡትን ተማሪዎች ስለአጠቃላይ ዓላማ እና አሞላል ማብራሪያ ከተሰጣቸው በኋላ በየግላቸው እንዲሞሉ ተደርገዋል፡፡ የፅሁፍ መጠይቆቹም በጥናቱ የመጨረሻ ክፍል በአባሪነት ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

## 3.4.የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂልን ክፍል ውስጥ አተገባበርን መፈተሽ ይሆናል፡፡ ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ በመጀመሪያ ከመናገር ክሂል ማስተማሪያ ስልቶች ጋር ግኑኝነት ያላቸውን ጥናታዊ ፅሁፍ (ሥራዎችን) በማፈለግ መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡ በመቀጠል በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች እያንዳንዱ መላሽ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጠውን ምላሽ በምልከታ ወቅት ከተገኘው መረጃ ጋር በማገናዘብ ተብራርተው ቀርበዋል፡፡ ስለዚህ አይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴዎችን በመጠቀም ከሁለቱም የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ ስራ ላይ የዋሉት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች በአባሪነት በመጨረሻ ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

### 4.1 የውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡ ከላይ በምዕራፍ ሦስት እንደተገለፀው ለዚህ ጥናት የሚሆን መረጃ የተሰበሰበው ለጥናቱ በተለዩ በአራቱም ትምህርት ቤቶች በሶስት ዙሮች ከተካሄደው የክፍል ውስጥ የንግግር ትግበራ ምልከታ፣ ለመምህራንና ለተማሪዎች ከቀረቡት የጽሑፍ መጠይቆች ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ከላይ ከተገለጹት የመረጃ ምንጮች የተሰባሰቡ መረጃዎች የጥናቱን ዓላማ መነሻ በማድረግ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 4.1.1. በቅድመ ንግግር በክፍል ውስጥ አተገባበር የተገኘ መረጃ ትንተና

የክፍል ምልከታ በአራቱም ሀደሮ ጡንጦ ወረዳ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች በሶስት ዙሮች ተከሄዷል፡፡ ምልከታውን ለማድረግ የዚህ ጥናት አጥኚ ለአስራ ሁለት ክፍለ ጊዜ ያህል በክፍል ውስጥ ተገኝቶ ምልከታ አድርጓል፡፡ በተለይ በቅድመ ንግግር፣ በንግግርና በድህረ ንግግር የንግግር ተግባራት ላይ ትኩረቱን በማድረግ መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ ከነዚህ መረጃዎች መካከል በቅድመ ንግግር የንግግር አተገባበር ዙሪያ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ተጠናቅሮ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡- በቅድመ ንግግር የክፍል ውስጥ አተገባበር ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ

| ተቁ | የክፍል ውስጥ ተግባራት | አዎን | | አይደለም | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | የንግግር መልመጃው ከመጀመሩ በፊት አላማው ተገልጾ ነበር? | 4 | 25 | 8 | 75 |
| 2 | ለተማሪዎች የቀረበው የንግግር ርዕስ ግልጽ ነበር? | 8 | 75 | 4 | 25 |
| 3 | ለንግግር የቀረበው ርዕስ የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ያገናዘበ ነበር? | 6 | 50 | 6 | 50 |
| 4 | የንግግር አተገባበር ቅደም ተከተል በቅድሚያ ተገልጾ ነበር? | 6 | 50 | 6 | 50 |
| 5 | ለንግግር የቀረበው ርዕስ ጉዳይ የተማሪዎችን ዕለታዊ ህይወት ወይም ከክፍል ውጪ ያለውን እውነታ የሚያመለክት ፈጠራ የታከለበት ነው? | 5 | 32.5 | 7 | 67.5 |
| 6 | ለአይናፋርና ፈሪ ተማሪዎች በተለይ ለተማሪዎች ባጠቃላይ የንግግር ልምምድ የሚሆን በቂ ጊዜ ተሰጥቷል? | | | 12 | 100 |
| 7 | የንግግር ትምህርቱ መሠረት ያደረገው የተማሪውን መጽሐፍ ነው? | 12 | 100 | | |

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው የ9ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን ንግግር በሚያስተምሩበት ወቅት በቅድመ ንግግር ምልከታ በተከታታይ በአራት ትምህርት ቤቶች በሶስት ዙሮች በተደረጉ ተከታታይ ምልከታዎች እንደታየው መምህራን የንግግር ትምህርት በቀጥታ ከማቅረባቸው በፊት ወጥ የሆነ አላማ በግልፅ አቅርበው የጀመሩት በቁጥር 4 (25%) ሲሆኑ አላማው ተሳስተው እንኳን ያልገለጹት አብዛኞቹ መምህራን ናቸው፡፡ ይህም በቁጥር 8(75%) የሚሆኑት ናቸው፡፡ አንድን ትምህርት ለማስተማር ዝግጅት አድርጐ ወደ ክፍል

የሚገባ መምህር ወጥ አላማ ሊኖረው፣ ዓላማውም ለሚያስተምራቸው ተማሪዎች በግልፅ ቋንቋ መግለፅ ግዴታው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥናት ያረጋገጠው 75% በጥናቱ የተካተቱት መምህራን በትምህርት ዝግጅታቸው ላይ አላማ ነድፈው ቢቀርቡም ባይቀርቡም ለተማሪ ተዳራሽ ያላደረጉ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መምህራን ለንግግር መልመጃነት የሚመርጧቸው ወይም ይዘዋቸው የሚመጡባቸው ርዕስ ጉዳዮች የተማሪዎቹን የቀደመ ዕውቀት፣ ባህል፣ ወግ፣ ፍላጎትና ዕድሜ የመሳሰሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች የትኩረት ነጥብ ያደረጉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት ለተማሪዎች ምንነቱ ግልፅ የሆነ ርዕስ ይዘው የቀረቡት 8(75%) ናቸው፡፡ የቀሩት 4(25%) ይዘውት የቀረቡት ርዕስ ጉዳይ ግልፅ አልነበረም፡፡ ተማሪዎች ንግግር ለማድረግ ሲቸገሩ ተስተውለዋል፡፡ አብዛኞቹ መምህራን ጊዜ ወስደው ግልፅ ርዕስ የመረጡ ቢሆንም የቀሩት መምህራንም አንድን የንግግር ርዕስ ከመምረጣቸው በፊት የተማሪዎቻቸውን የቀደመ ዕውቀትና የርዕሱ ግልፅነት ከግምት በማስገባት ከተገቢ ማብራሪያ ጋር ርዕሱን ካላቀረቡ ነገሮች አደናጋሪ መሆናቸው አይቀሬ ይሆናል፡፡ የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር መምህራን ተናባቢ ርዕስ ጉዳዮችን ከመምረጥ አንፃር በርከት ያሉ መምህራን የተሻለ ግንዛቤ ኖሮኣቸው ግልፅ ርዕስ ጉዳይ የመረጡ ቢሆንም ጥቂት መምህራን ግልፅ ርዕስ የላቸውም ይህም ቢሆን መታረም ያለበት ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡ 25% ለጥናት ስለተመረጠ አነሰ እንጂ የአንድ ክፍል ተማሪዎች ሁሉ ግልፅ ባልሆነ ርዕስ ጉዳይ መቸገራቸውን ያሳያል፡፡ ስለዚህ የርዕስ ጉዳይ ግልፅ ያለመሆን ችግር አለ ማለት ነው፡፡

ሌለው የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ግምት ውስጥ ያስገባ ርዕስ ጉዳይ በንግግር ያቀረቡ 6(50%) ሲሆኑ የቀረበው ርዕስ ጉዳይ ምንም እንኳን ርዕሱ ለንግግር ግልፅ ቢሆንም የቀደመ ዕውቀትን መሠረት ያላደረገ 6(50%) ሆኖ ቀርቧል፡፡

ትምህርት በባዶ መሙላት ሳይሆን ባለ ነገር ላይ መጨመር እንደሆነ በርካታ ምሁራን ይስማማሉ፡፡ እዚህ ላይ ርዕሱ ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ ቢሆንም በርዕሱ ዙሪያ ለንግግር የሚሆን መረጃ ማግኛ ምንጭ ግልፅ ስላልሆነ ተማሪዎች ሲቸገሩ ታይተዋል፡፡ በተለይ ከዕውቀት ደረጃቸው አንድ ደረጃ ከፍ ያለ ርዕስ ሲቀርብ ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶ ከተገቢ የመረጃ ምንጮች መረጃ መሰብሳቢያ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በዚህ መሠረት ከቀረቡት ክፍሎች ግማሽ ያህሉ የቀረበላቸው ርዕስ ጉዳይ ካላቸው ዕውቀት በላይ ነው፡፡ ይህም ሊሻሻል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

የንግግር አተገባበር የራሱ አካሄድ አለው፡፡ እንዴት መጀመር፣ እንዴት መቀጠልና መጠቃለል እንዳለበት የማያሻማ መመሪያና የአካሄድ ቅደም ተከተል ሊሰጠው ይገባል፡፡ ይህን በተመለከተ

ይህ ጥናት ያረጋገጠው 6(50%) መምህራን ግልፅና የማያሻማ የንግግር አተገባበር ቅደም ተከተልን በተመለከተ በጥንቃቄ መመሪያ ያቀረቡ ሲሆን ሌሎቹ በጠቀሱት ርዕስ ጉዳይ ንግግር እንዲያደርጉ ከመግለፅ ያለፈ ግልፅ መመሪያና የአተገባበር ቅደም ተከተል ሲሰጡ አልታዩም። ይህም በቁጥር 6(50%) የሆኑትን ያጠቃልላል። ንግግር የአካሄድን ቅደም ተከተል የሚያሳይ የማያሻማ መመሪያ ካልተሰጠው መደናጋገርና ጊዜ ማባከን እንጂ ትምህርት አይሆንም። ማንኛውም ውስብስብ ርዕስ ጉዳይ ቢሆን በቂና ግልፅ የአተገባበር መመሪያና ቅደም ተከተል ከተሰጠው ሊተገበር ይችላል። በሌላ በኩል ምንም አይነት ግልፅ ርዕስ ጉዳይ ቢቀርብ በበቂ የአተገባበር መመሪያና ቅደም ተከተል ካልታገዘ ፋይዳ ያለው ንግግር አይሆንም። ስለዚህ ንግግር ሁልጊዜ የአተገባበር ቅደም ተከተል ያለው መመሪያ ያስፈልገዋል። በዚህ መሠረት ይህ ጥናት ያገኘው በቂና ግልፅ መመሪያና የንግግር አካሄድ ቅደም ተከተል በግልፅ ከማቅረብ አንፃር በትምህርት ቤቶች ውስጥ ችግር ያለ መሆኑን ነው።

ለንግግር የቀረበው ርዕስ ጉዳይ የተማሪዎችን ዕለታዊ ህይወት የሚያንፀባርቅ እንዲሆን በማድረግ ፈጠራ የታከለበት ከመሆን አንፃር ጥቂት ቁጥር ያላቸው መምህራን ፈጠራን የሚቀሰቅሱና ተማሪዎች እውናዊ ህይወታቸውን በክፍል ውስጥ በፈጠራ በመታገዝ እንዲያመጡ ያደረጉ በቁጥር 5 (32.5%) ብቻ ናቸው። በርካታ ተማሪዎች እንዲተገብሩት የተሰጣቸው ፈጠራ ያልታከለበት በማዕከላዊነት የቀረበውን ርዕስ ጉዳይ እንዳለ በመቀበል ነው። ይህ አካሄድ የተማሪዎችን የመመራመር አቅም ይገድባል። ተማሪውን ለዕውኑ ዓለም ማህበረሰባዊ ተራክቦ አያዘጋጅም።

ስለዚህ በአብዛኞቹ በቁጥር 7(67.5%) ተማሪዎች ፈጠራ አይሞከርም፤ አይተገበርምም። በዚህ መሠረት በትምህርት ቤቶች የንግግር ክሂል ቢተገበር ተማሪዎችን ለማህበራዊ ተራክቦ የሚያዘጋጁና ለፈጠራ የሚጋብዙ ርዕስ ጉዳዮች እምብዛም እንደማይቀርቡ ጥናቱ አረጋግጧል።

በአንድ ክፍል ውስጥ ሦስት አይነት ተማሪዎች የሚገኙ መሆኑ ተደጋግሞ የተባለ ዕውነት ነው። በንግግር ክፍለ ጊዜ ፋሪና አይናፋር ተማሪዎች ያጋጥማሉ። እነዚህን ተማሪዎች ወደ ሌሎቹ የክፍል ጓደኞቻቸው የቀረበ የክሂል አቅም እንዲኖራቸው ለማድረግ በቂና ከሌሎቹ አንፃር ሲታይ ተመጣጣኝ የንግግር ልምምድ ወይም ፍርሃት መቀነሻ በቂ የሚባል ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት መሠረት አንድም መምህር ለፈሪና አይናፋር የተለየ ጊዜ የሰጠ መምህር ወይም ክፍል የለም። አራቱም መምህራን ሁሉም ተማሪዎች በተመሳሳይ ጊዜ ዝግጅት በማድረግ ወደ ንግግር አተገባበር ለመግባት ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ አድርገዋል። ከዚህ የተነሳ በሁሉም ክፍሎች ላለመናገር የታቀቡ ፈሪዎች፣ ሲናገሩ በእጃቸው የያዙት ወረቀት

መንቀጥቀጣቸውን የሚያሳብቅባቸውና ንግግር እንደጀመሩ በላብ የሚጠመቁ ተማሪዎች ታይቷል፡፡ የዚህ ችግር ምንጩ መምህራን ለንግግር ደጋግሞ መላማመድ ጊዜ ያለመስጠታቸው ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ጥናቱ የደረሰበት ዕውነት ለንግግር ልምምድ በቂ ጊዜ ያለመስጠቱንና ተማሪዎች በፍርሃትና በአይናፋርነት ተለይተው ድጋፍና በቂ የልምምድ ጊዜ ያልተሰጣቸው መሆኑ ነው፡፡

በክፍል ውስጥ ለንግግር ክሂል አተገባበር የሚቀርብ ርዕስ ጉዳይ መሠረቱ የተማሪው መጽሐፍ መሆን አለበት፡፡ የተማሪው መጽሐፍ ደግሞ መሠረቱ ሀገሪቱ የምትከተለው ስርዓተ ትምህርት ነው፡፡ ከታዩት 12 ክፍለ ጊዜያት በሁሉም በቁጥር 12(100%) የተማሪውን የ9ኛ ክፍል መጽሐፍ መሠረት ያደረገ የንግግር ርዕስ ቀርቧል፡፡ ይህ የሚያሳየን ሁሉም ተመራጭ መምህራን ስርኣተ ትምህርቱን ማዕከል ያደረገ ርዕስ ጉዳይ ይዘው መቅረባቸውን ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ርዕስ አመራረጡ ሀገራዊ መሠረት ያለው ወጥ የንግግር ዕድገት ያለው አካሄድ መሆኑን ነው፡፡

*ሠንጠረዥ ፫፡-* **ለመምህራን ከቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ የተሰባሰበ ቅድመ ንግግር የሚመለከት መረጃ**

| ተቁ | ቅደመ ንግግር ተግባራት | የመምህራን ምላሽ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አብዛኛውን ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በፍጹም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | የንግግር መልመጃ ከመጀመሪያ በፊት የንግግሩን ዓላማ ይገልፃሉ? | 1 | 25 | 1 | 25 | 1 | 25 | 1 | 25 |
| 2 | ለተማሪዎች መርጠው የሚያዘጋጁት ርዕስ ግልፅ ነበር? | 2 | 50 | 1 | 25 | 1 | 25 | | |
| 3 | ለተማሪዎች የቀደመ ዕውቀት የሚመጣጠን ርዕስ መርጠው ያቀርባሉ? | | | 2 | 50 | 2 | 50 | | |
| 4 | ለተማሪዎች የንግግር መመሪያና ግልፅ ቅደም ተከተል አስቀድመው ይናገራሉ? | 1 | 25 | 1 | 25 | 1 | 25 | 1 | |
| 5 | ለተማሪዎች የሚመርጧቸው ርዕስ ጉዳዮች የተማሪዎችን ዕለታዊ ህይወትና ፈጠራን ያማከሉ ናቸው? | | | 1 | 25 | 3 | 75 | | |
| 6 | ለፈሪና አይናፋር ተማሪዎች በቂ የመለማመጃ ጊዜ ተሰጥቷል? | | | | | 2 | 50 | 2 | 50 |
| 7 | ለንግግር የሚመርጧቸው ርዕስ ጉዳዮች የተማሪ መጽሐፍን ያማከላሉ? | 3 | 75 | 1 | 25 | | | | |

ከላይ ከሠንጠረዡ ማየት እንደሚቻለው በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገባቸው መምህራን የንግግር መልመጃ ከማቅረባቸው በፊት የመልመጃውን ዓላማ በትክክል ገልጾ ከመጀመር አንፃር ከፍተኛ ክፍተት ታይቶባቸው እያንዳንዱን የንግግር ትምህርት ዓላማ በመግለፅ የሚጀምረው 1(25%) ሁልጊዜ አቀርባለሁ ብለዋል፡፡ 1(25%) ደግሞ አልፎ አልፎ ባያደርጉም አብዛኛውን ጊዜ ያደርጋሉ፡፡ ከሞላ ጎደል 2(50%) መምህራን ዓላማ ገልጸው ይጀምራሉ ብሎ ማጠቃለል የሚቻል ሲሆን የቀሩት 2(50%)፣ 1(25%) አልፎ አልፎ አላማ የሚገልፁ ሲሆን 1(25%) አላማ መቼም የማይገልጹ ያለ ዓላማ የንግግርን ትምህርት የሚያቀርቡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በዚህ መሠረት በክፍል ምልከታው እንደተረጋገጠው ያለ ዓላማ ትምህርት መስጠት አግባብነት የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህም በ2 (50%) መምህራን ያለ ዓላማ የንግግር ትምህርት መቅረቡ እንደ ችግር ወይም የትምህርቱ ክፍተት ሆኖ መታየት ያለበት ነው፡፡

ለክፍል ተማሪዎች ግልፅ የንግግር ርዕስ መርጦ ከማቅረብ አንፃር 2(50%) አቀርባለሁ ያሉ ሲሆን 1(25%) ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ መርጣለሁ ብለዋል፡፡ አንድ(25%) መምህር ግን አልፎ አልፎ ግልፅ ርዕስ መርጣለሁ ብለዋል፡፡ በዚህ መሠረት 3(75%) በተቀራራቢነት ለተማሪዎች ቀረቤታና ግልጽነት ያለው ርዕስ እንደሚመርጡ መግለፃቸው የተሻለ መሆኑ ተደርሶበታል፡፡

ለተማሪዎች የቀደመ ዕውቀት የሚመጣጠን ርዕስ መርጦ ከማቅረብ አንፃር 2(50%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ የሚመርጡ መሆኑን ሲገልጹ፣ 2(50%) መምህራን ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚመርጡ ገልጸዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው አንድ መምህር ይዘትን መርጦ ሲያደራጅ የተከታታይነትን የአደረጃጀት መርህ መከተል ግዴታ ነው፡፡ ለተማሪዎች የቀደመ ዕውቀት መመጣጠን ባለፈው ካቆሙበት ዛሬ መቀጠልን የሚያመለክት እንደመሆኑ መጠን ሁልጊዜ ለቀደመ ዕውቀት የሚመጣጠን ርዕስ የሚያቀርቡ መምህራን መጥፋታቸው በደካማነት የተያዘ ክፍተት ሲሆን ፈጽሞ የማይሰጡ መምህራን ያለመኖራቸው ደግሞ በጥንካሬው የሚያዝ ነው፡፡

ለተማሪዎች ግልጽ የንግግር አካሄድ መመሪያና ቅደምተከተል ገልጸው ትምህርት የሚጀምሩ መምህራን 1(25%) ሁልጊዜ መመሪያና ቅደምተከተሉን አሳያለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ 1(25%) መምህር ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ አደርጋለሁ ብለዋል፡፡ 1(25%) መምህር በበኩሉ አልፎ አልፎ ግልፅ መመሪያና የንግግር አካሄድ ቅደም ተከተል አሳይቼ አስጀምራለሁ ብለዋል፡፡ 1(25%) መምህር በተቃራኒው ለንግግር ተማሪዎቼ ሲቀርቡ ፈጽሞ መመሪያ አልነግራቸውም፡፡ ቅደም ተከተሉንም አላሳያቸውም ብለዋል፡፡ የንግግር አተገባበሮች ውይይት፣ ክርክር፣ ጭውውት ወዘተ ተማሪዎች በራሳቸው ቡድን የሚፈጽሟቸው ቢሆኑም ያለ ግልፅ መመሪያና የአፈጻጸም ቅደም ተከተል የሚሆኑ አይደሉም፡፡ በዚህ መሠረት “አልፎ አልፎ መመሪያ እሰጣለሁ” የሚሉና

“ፈጽሞ መመሪያ አልሰጥም” የሚሉ የመምህራን መልሶች ለንግግር አተገባበር ግዴለሽ አመለካከት ያላቸው መምህራን መኖራቸውን የሚያሳይ አፈጻጸም ነው። ይህም የክሂሉ አተገባበር ከፍተኛ ክፍተት ነው።

ለተማሪዎች የሚዘጋጁ የንግግር ርዕስ ጉዳዮች የተማሪዎችን ዕለታዊ ህይወት የሚያንፀባርቁ፣ ለፈጠራ የሚያነሳሱ ከማድረግ አንፃር 1(25%) ብቻ አብዛኛውን ጊዜ አደርጋለሁ በሚል የመለሱ ሲሆን 3(75%) መምህራን ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል። ተማሪው የራሱን የዕለት ተዕለት ህይወት የሚያንፀባርቅ ርዕስ ጉዳይ ካገኘ በፍቅር ይከታተላል፤ ይሳተፋል። የሌላ አካል ከሆነ ግን ያለመሳብ፣ ለትምህርቱ ፍቅርና ተመስጦ ማጣት ይታይበታል። የራሱን ህይወት የማያሳየውን ትምህርት ወዶት ሳይሆን ተገዶ ነው የሚማረው። ቋንቋ በባህርዩ ፈጠራን የሚያበረታታ ከሆነ ሳቢነት ይኖረዋል። በዚህ መሠረት ጥናቱ የደረሰበት እውነታ ቢኖር ተማሪዎች ፈጥረው ያለውን እውነታ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን በፈጠራ የማበልፀግና ዕለታዊ ህይወቱን የሚያሳይ ርዕስ ጉዳይ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዳልተፈጠረለት ነው።

በአንድ ክፍል ለመማር የገቡ ተማሪዎች ሁሉም ትምህርቶች የመሳተፍ ዕድል ሊኖራቸው ይገባል። ሆኖም አንዳንድ ተማሪዎች እራሳቸውን የመደበቅ፣ የመፍራትና አይናፋር የመሆን ችግር የሚታይባቸው ተማሪዎች ይኖራሉ። መምህራን ደግሞ ለነዚህ አይናፋርና ፈሪ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ቀርበው ከመነጋገር በፊት የመለማመጃ ጊዜ ሊያገኙ ይገባል። ከዚህ አንፃር ለነዚህ አይነት ተማሪዎች የመለማመጃ ጊዜ ሁልጊዜ የሚያዘጋጅ አንድም መምህር የለም። 2(50%) መምህር አልፎ አልፎ የመለማመጃ ሁኔታ አመቻቻለሁ ያሉ ሲሆኑ አብዛኞቹ መምህራን 2(50%) በፍጹም አላዘጋጅም የሚል መልስ ሰጥተዋል። ይህ ማለት 50% አልፎ አልፎ ማዘጋጀትና 50% ፈጽሞ አለማዘጋጀት በጥቅሉ ሲታይ አይናፋርና ፈሪ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በዳፋርና በተናጋሪ ተማሪዎች የተዋጡበት ሁኔታ እንዳለ በግልፅ ይታያል። ይህ ጥናቱ የደረሰበት እውነታ የሚያሳየው የመማሪያ ክፍሉ በደፋር ተማሪዎች ተፅዕኖ ስር የወደቀ መሆኑንና መምህራንም ይህን ችግር፣ እነዚህን አይናፋርና ፈሪ ተማሪዎች ወደ ጎን በመተው ከፈጣን ተናጋሪ ተማሪዎች ጋር ብቻ በመሆን የንግግር ክሂሉን በጋራ ለማሳደግ ከባድ መሰናክል መሆኑን ያሳያል።

በንግግር የሚቀርቡት ርዕስ ጉዳዮች መሠረት ማድረግ ያለባቸው ሥርዓተ ትምህርቱን መሆን አለበት። በክፍል ውስጥ የሚገኘው የሀገሪቱ ስርዓተ ትምህርት ወካይ የተማሪው መጽሐፍ ነው። ለተማሪዎች የሚቀርብ የንግግር ትምህርትም መሠረቱን በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ላይ ማድረግ አለበት። ለክፍል የንግግር መልመጃ ሲመርጡ የተማሪን መጽሐፍ መሠረት

ከማድረግ አንፃር ተጠይቀው ሁልጊዜ አደርጋለሁ ያሉት 3(75%) ሲሆኑ፣ አብዛኛውን ጊዜ አደርጋለሁ ያለው 1(25%) ነው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይም ሁሉም በዚህ ጥናት የተተኮረባቸው መምህራን የመማሪያ መጽሐፍን የመነሻ ነጥቦ አድርገው የተነሱ መሆኑን ያሳያል፡፡ መምህራኑ ለክፍሉ የተመደበውን መርሀ-ትምህርት ከፍ ሲልም ስርዓተ ትምህርቱን ማዕከል ያደረጉ ስለሆነ በጥንካሬው የተደረሰበት ድምዳሜ ነው ማለት ነው፡፡

ሠንጠረዥ 4፡- በቅድመ ንግግር የመናገር ክሂል ተግባራት የክፍል ውስጥ አተገባበር የተማሪዎች ምላሽ ትንተና

| | | ሁልጊዜ | | አብዛኛውን ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | አይደረግም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1 | ንግግር ከመጀመራችሁ በፊት መምህሩ ግልፅ አላማ ያቀርባሉ፡፡ | 8 | 7 | 36 | 32 | 40 | 36 | 28 | 25 |
| 2 | መምህሩ ለንግግር የሚመርጡት ርዕስ ጉዳይ ግልፅ ነው፡፡ | 30 | 27 | 42 | 37.5 | 20 | 18 | 20 | 18 |
| 3 | የሚመረጡት ርዕስ ጉዳዮች የንግግር ችሎታችሁን ያማከሉ ናቸው፡፡ | 10 | 9 | 60 | 54 | 30 | 26 | 12 | 11 |
| 4 | ንግግር ከመጀመራችሁ በፊት ግልፅ መመሪያና የአቀራረብ ቅደም ተከተል ይሰጣችኋል፡፡ | 20 | 18 | 36 | 32 | 44 | 39 | 12 | 11 |
| 5 | ለንግግር የሚሰጠው መመሪያ አሻሚነት ያለው ነው፡፡ | 12 | 11 | 44 | 39 | 36 | 32 | 20 | 18 |
| 6 | ለንግግር የሚመረጡት ርዕሰ ጉዳዮች ከተማሪዎች ህይወት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ | 8 | 7 | 28 | 25 | 48 | 43 | 28 | 25 |
| 7 | የንግግር መለማመጃ በቂ ጊዜ ይሰጣችኋል፡፡ | | | 30 | 28 | 70 | 61 | 12 | 11 |
| 8 | በክፍል ውስጥ ላሉት መናገር ለማይደፍሩና ለአይናፋር ተማሪዎች በቂ የልምምድ ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡ | | | | | 90 | 80 | 22 | 20 |

ከላይ ባለው ሠንጠረዥ የቀረበው የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ የሚከተለውን የክፍል ውስጥ የቅድመ ንግግር ሂደቶችን ያሳየናል፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በምልከታውና ከመምህራን መጠይቅ የተገኘው መረጃ አብዛኞቹ መምህራን ለተማሪዎች አላማ ገልፃው ንግግር እንደማያስጀምሩ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ 8(7%) ተማሪዎች ሁልጊዜ አላማ ይነገራናል ሲሉ 36(32%) ተማሪዎች ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ አላማው በቅድሚያ ተነግሮን የንግግር መልመጃ ይሰጠናል ያሉ ናቸው፡፡ “ሁልጊዜ” ና “አብዛኛውን” ጊዜ ከጽንሳ ሀሳብ አንፃር ተቀራራቢነት ያላቸው ስለሆኑ ሁለቱንም ያሉት ተማሪዎች በድምሩ 44(39%) ናቸው፡፡ አቀራረቡ ማለትም መምህራን አላማውን በማስቀደም የንግግር መልመጃ የማቅረባቸው ሁኔታ ከሚገባው በታች መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህን እውነታ የሚያጠናክረው ደግሞ አልፎ አልፎ ይቀርባል ያሉት ተማሪዎች 40(36%) መሆናቸው እና አይደረግም ያሉት 28(25%) ተማሪዎች መሆናቸው ነው፡፡ 61% የሚሆኑ ተማሪዎች ዓላማን አስቀድሞ ማቅረብ ያልተለመደ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል ለክፍል ውስጥ የንግግር መልመጃ የሚመረጠው ርዕስ ለተማሪዎቹ ግልፅ ከመሆን አንፃር ከተጠየቁት ተማሪዎች መካከል 30(27%) ተማሪዎች ሁልጊዜ ግልፅ ርዕስ ይመረጥልናል ሲሉ 42(38%) ተማሪዎች ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ግልፅ ርዕስ ይመረጣል ብለዋል፡፡ አልፎ አልፎ የሚመረጠው የንግግር ርዕስ ግልፅ ነው ያሉት ቁጥራቸው 20(18%) ሲሆን ግልፅ ርዕስ አይመረጥም ያሉም አሉ፡፡ ግልፅ ርዕስ አይመረጥም ያሉት 20(18%) ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ለንግግር የሚመረጠው ርዕስ ጉዳይ ከሞላ ጐደል ግልፅ ነው፡፡ እዚህ ላይ ሀሳብ ከመረዳት አንፃር ያለው የተማሪዎች የፍጥነት ልዩነትም ከግምት ውስጥ የሚገባ ይሆናል፡፡

የንግግር መልመጃ ከመሰጣቱ በፊት ግልፅ የንግግር መመሪያና ቅደም ተከተል ከመናገር አንፃርም ተማሪዎች የተለያየ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ሁልጊዜ ይሰጣል ያሉት 20(18%) ሲሆኑ አብዛኛውን ጊዜ ይሳጣል ያሉት ደግሞ 36(32%) ናቸው፡፡ አልፎ አልፎ ይሰጠናል ያሉት 44(39%) ሲሆኑ ግልፅ መመሪያ አይሰጣንም ያሉትም ቁጥራቸው የዋዛ አይደለም፡፡ 12(11%) ናቸው፡፡ ይህ አሃዛዊ መረጃ የሚያመለክተው የመምህራን ለንግግር መልመጃ ግልፅ መመሪያና የአሠራር ቅደምተከተል የመስጠት ሁኔታ ችግር ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው አብዛኛው 50% የመልመጃ መመሪያዎች አሻሚነት እንዳላቸው ነው፡፡ አሻሚ መልመጃ ደግሞ በ9ኛ ክፍል ደረጃ ላይ ላላ ለምርምር ቅርብ ላልሆነ ተማሪ ጊዜና ጉልበቱን የሚጨርስ ንግግርን እንዲሸሽ የሚያደርግ መሰናክል ነው፡፡

ሌላ የሚመረጠው ርዕስ ጉዳይ ከተማሪዎች ዕለታዊ ህይወትና ኑሮ ጋር ቁርኝትና የጠበቀ ትስስር የሌላው መሆኑን የሚያሳዩ ምላሾች ተገኝተዋል፡፡ ርዕስ ከህይወታችን ጋር ቁርኝት ያለው ነው ያሉት 8(7%) ተማሪዎች ብቻ ሲሆኑ፣ ርዕስ ጉዳዮቹ አልፎ አልፎ ህይወታችንን ይነካሉ ያሉት 28(25%) ናቸው፡፡ ይህን ጉዳይ ከሞላ ጎደለ በአዎንታ የመለሱት 36(32%) ተማሪዎች ብቻ ሲሆኑ 68% በቁጥር 76 የሚሆኑ ተማሪዎች በአሉታ መልሰዋል፡፡ 48(43%) ተማሪዎች አልፎ አልፎ ሲሉ 28(25%) የሚሰጡን ርዕሶች ከህይወታችን ጋር ቀረቤታ የሌላቸው ናቸው ብለዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው መምህራን በአጠቃላይ ደረጃ የተዘጋጁት መፃህፍት የያዙትን መረጃ ለተማሪዎቹ ኑሮ፣ ባህል፣ አካባቢ … አመቻችተው የማያቀርቡ መሆኑን ነው፡፡

ለንግግር መልመጃ የሚሰጠው ጊዜ ተማሪዎች በበቂ ሁኔታ እንዲናገሩ የሚፈቅድ መሆን አለመሆኑን ሲጠየቁ ሁልጊዜ በቂ ጊዜ ይሰጣል ያለ አንድም ተማሪ የለም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ይሰጠናል ያሉት 30(28%) ተማሪዎች ሲሆኑ አልፎ አልፎ በቂ ጊዜ ይሰጠናል 70(61%)፣ ፈጽሞ አይሰጠንም ለንግግር መልመጃ በቂ ጊዜ ተመድቦ አያውቅም ያሉት 12(11%) ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት ለንግግር በቂ የሆነ ጊዜ እንደማይመደብ 72% ተማሪዎች የተስማሙበት ነው፡፡ በቂ የንግግር ጊዜ ካልተመደበ ደግሞ የተማሪዎችን የንግግር ችሎታና አቅም ለመመዘን፣ ተማሪዎችን ለእውኑ ዓለም ንግግር የማብቃታችንን አቅም መለኪያ ምንም ዘዴ አይኖርም ማለት ነው፡፡

በክፍል ውስጥ ሦስት አይነት ተማሪዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ በተለይ በንግግር ወቅት ላብ ላብ የሚላቸው ፋሪዎችና ድምፅቸው እንዳይሰማ የሚቆጣጠሩ አይናፋሮች ብዙ ጊዜ ይኖራሉ፡፡ ለእነዚህ አይነቶቹ ተማሪዎች ደግሞ በቂ የንግግር ልምምድ መስጠት አስፈላጊነቱ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ በዚህ መሠረት ለእንደዚህ አይነት ተማሪዎች የተሰጠው ጊዜ እጅግ ዝቅተኛ እንደሆነ ጥናቱ ደርሶበታል፡፡ 90(80%) ተማሪዎች አልፎ አልፎ ለፈሪና አይናፋር ተማሪዎች የልምምድ ጊዜ ይሰጣል ሲሉ 22(20%) ተማሪዎች ደግሞ አይሰጥም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከላይ በክፍል ምልከታውም ሆነ ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያጠናክረው ይህንኑ እውነታ ነው፡፡

ከላይ የቅድመ ንግግር ዝግጅት ወቅትን በተመለከተ የተሰባሰበው አጠቃላይ መረጃ የሚያመለክተው የቅድመ ንግግር የክፍል ውስጥ ተግባራት እጅግ ከፍተኛ የሆነ ትኩረት በሚፈለግ ደረጃ የተጎዱ መሆናቸውን ነው፡፡

### 4.1.2. በንግግር ጊዜ የንግግር አተገባበር ዙሪያ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና

ከላይ በክፍል 4.1.4 በቅድመ ንግግር ጊዜ በክፍል ውስጥ የነበረውን ሁኔታ አጥኚው ካደረገው ተደጋጋሚ የክፍል ምልከታ፣ ለመምህራንና ለተማሪዎች ተዘጋጅተው ከቀረቡት የጽሑፍ መጠይቆች የተገኘው መረጃ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ ንግግር በሚደረግበት ወቅት ያለውን ሁኔታ አስመልክተው ከቀረቡት መጠይቆች የተሰበሰበው መረጃ በክፍል ምልከታ፣ ከመምህራን መጠይቅና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በቅደም ተከተል ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 5፦ በንግግር ጊዜ ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

| ተቁ | በንግግር ወቅት የክፍል ውስጥ የንግግር አተገባበር | አዎን | | አይደለም | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 8 | ለንግግር የተመደበው ጊዜ ለንግግሩ በቂ ነበር? | 6 | 50 | 6 | 50 |
| 9 | ንግግሩ ላይ ሁሉም ተማሪዎች ተሳታፊ እንዲሆኑና በጉበዝ ተማሪዎች ተፅዕኖ ስር እንዳይወድቅ መምህሩ ጥንቃቄ አድርገዋል? | 4 | 25 | 8 | 75 |
| 10 | መምህሩ የተማሪዎች የንግግር መልመጃ ተግባር በትኩረት ጊዜ ሰጥተው ይከታተላሉ? | 12 | 100 | | |
| 11 | በንግግር ወቅት ተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች መምህሩ ሳያልፉ እንዲታረሙ ያደርጋሉ? | 5 | 37.5 | 7 | 62.5 |
| 12 | ከስዕል፣ ከሠንጠረዥ፣ ከፎቶ፣ ከጋዜጣ… የተዘጋጀ ንግግር የቀረበበት ሁኔታ አለ? | | | 12 | 100 |
| 13 | የተማሪዎቹ ንግግር ራሳቸው በመረጡት ርዕስ ዙሪያ ቀርቧል? | 4 | 25 | 8 | 75 |
| 14 | ተማሪዎች ሳይሸማቀቁ ነፃ ሆነው ንግግራቸውን እንዲያቀርቡ ክፍሉ ከተራ ጣልቃገብነት የፀዳ ነበር? | 6 | 50 | 6 | 50 |
| 15 | የንግግሩ አካሄድና መምህሩ በዕቅድ ደረጃ የነደፉት አብረው የሚሄድ ነበር? | 4 | 25 | 8 | 75 |

ሠንጠረዥ 8 የሚነግረን አጥኚው በክፍል ውስጥ ንግግር እየተተገበረ ባለ ሰዓት የተመለከተውን እውነታ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ለንግግር የተመደበው ጊዜ ለመናገር ለተዘጋጁ ተማሪዎች ወይም ቡድኖች በቂ ነበር? በሚል ለቀረበው ጥያቄ የተገኘው መልስ አዎ የሚል 6(50%) ሲሆን በቂ አይደለም 6(50%) ነው፡፡ ከአስራ ሁለት ምልከታ ከተደረገባቸው ክፍሎች ስድስቱ በቂ የጊዜ እቅድ ተደርጐባቸው ንግግር ተደርጐ፣ ጥያቄ ተጠይቆና ማስተካከያዎች ተሰጥተው የተጠናቀቁ

ሲሆኑ 6(50%) ደግሞ ንግግሩ ሳያልቅ ሰዓት አልቆባቸዋል፡፡ ስለዚህ ለእርማትና ለጥያቄ ዕድል የሚሆን ሰዓት አላገኙም፡፡ ይህ የሚያሳየው በሁሉም ክፍሎች ተመጣጣኝ ዝግጅት ያለመደረጉንና የሰዓት አጠቃቀም ጉራማይሌ መልክ መታየቱን ነው፡፡

የተማሪዎች ተሳትፎ በተመለከተ ሁሉም ተማሪዎች ሳይታቀቡና ንግግሩ በጎበዝ ተማሪዎች ተጽዕኖ ስር ሳይወድቅ ስለማድረጋቸው የተደረገው ምልከታ የታዘበው 8(75%) ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የንግግር ዕድል መሰጠቱን ሲያመለክት 4(25%) ንግግሩ በጎበዝ ተማሪዎች ቁጥጥር ስር ከመዋሉም በላይ ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆኑ ተማሪዎች ተትተው ሲታለፉ ታይቷል፡፡ ትምህርት የያንዳንዱ ሰው ስኬት ድምር ውጤት የሚጠበቅበት እንጂ ጥቂት ፊት የወጡ ፈጣን ተማሪዎች የሚጫኑት አይደለም መሆንም የለበትም፡፡ በዚህ መሠረት ሀሳብ ዙሪያ በክፍል የተገኘው ውጤት አመርቂ ቢሆንም ሥራ የሚጠይቅ የቀራ ነገር መኖሩን የሚጠቁም ክፍተትም አለ፡፡

በየክፍሉ የተገኙት መምህራን የተማሪዎችን ንግግር ጊዜ ሰጥተው በትኩረት መከታተላቸውን የሚጠቁም ምልከታ ተደርጓል፡፡ ይህም ክፍሉን ለመቆጣጠርም ሆነ የተማሪዎችን የንግግር ክፍተት ለማወቅ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ የምልከታ ቁጥር 12 የሆነው 4ቱን መምህራን በሶስት ዙር አጥኚው ስላገኛቸው ነው፡፡

በንግግር ወቅት የሚፈጸሙ ስህተቶችን መምህሩ ትኩረት ሰጥተው እንዲታረሙ ከማድረግ አንፃር የታየው 5(37.5%) የሆኑ መምህራን ስህተቶችን በመለየት በስህተት ፋፃሚዎቹ፣ በጓደኞቻቸው ወይም መምህሩ በራሳቸው የስህተቱን አይነት ሲያርሙ ታይተዋል፡፡

በርካታ መምህራን 7(62.5%) የሚሆኑት ካለው የጊዜ ጥበትና ንግግሩን ለሁሉም ቡድኖች ለማዳረስ በማሰብ በሚመስል መልኩ ስህተቶችን እንዳሉ ሲያልፉኣቸው ተስተውለዋል፡፡ የስህተት ያለመታረም የቋንቋውን ስርኣት ከማበላሸቱም በላይ ለተማሪዎች የወደፊት የተግባቦት ሂደት ችግር የሚያስከትል ይሆናል፡፡

በንግግር አቀራረብ ሂደት ከስዕል፣ ከሠንጠረዥ፣ ከፎቶ፣ ከጋዜጣ ወዘተ የተዘጋጀ ንግግር መኖሩን ለማረጋገጥ የተደረገው ምልከታ ያረጋገጠው አንድም መምህር ተማሪዎች ከመሰል ምንጮች መረጃ በማመንጨት አቀናጅተው ንግግር እንዲያደርጉ ያላዘጋጃ መሆኑን 12(100%) አለማድረጋቸውን አጥኚው ተመልክቷል፡፡ ይህ የሚያመለክተው የተማሪዎችን የፈጠራና የመመራመር አቅም የሚገድብ ደካማ አፈጻጸም የተመዘገበበት ሁኔታ ሆኗል፡፡

በሌላም በኩል ለውይይት፣ ክርክር፣ ጭውውት … የሚሆን ርዕስ ጉዳይ ከራሳቸው በማዘጋጀት ውይይት ያደረጉት በ4(25%) ክፍሎች ሲሆን የቀሩት 8(75%) መምህራን መርጠው በሚያቀርቧቸው ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ ንግግር ሲያደርጉ ተስተውለዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው ተማሪዎች በራስ የመተማመን አቅማቸው እንዳይጐለብት ሁልጊዜ በመምህራን ርዕስ ጉዳይ ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ የሚያደርግ ክፍተት ያለበት አካሄድ መሆኑ ተደርሶበታል፡፡ ተማሪዎች በራሳቸው ርዕስ ሲመርጡ መረጃ ለመሰብሰብ የሚወሰድባቸውን ረጅም ሰዓት በመቀነስ በአጭር ጊዜ ዝግጅት አድርገው ንግግር እንዲያቀርቡ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ የተማሪዎች ንግግር ከተማሪዎች እና ከመምህራን አላአስፈላጊ ጠልቃገብነት ነፃ ሆኖ ከማቅረብ አንፃር የታየው የተቀላቀለ ነገር ነው፡፡ 6(50%) ክፍሎች የታየው መምህሩና ሌሎች ተማሪዎች ንግግሩ እንዲቆራረጥ በማድረግ የማስተካከያ ሀሳብ ሲሰጡ የተስተዋሉ ሲሆን በቀሩት 6(50%) ክፍሎች ደግሞ ንግግር አቅራቢዎች አጠናቀው ለጥያቄና አስተያየት ክፍት እስኪያደርጉ ድረስ በፀጥታ ተከታትለዋል፡፡ ጠልቃገብነት ሀሳብ እንዲበተንና መደነጋገር እንዲመጣ የሚያደርግ ስለሆነ አይደገፍም፡፡

በመምህሩ ተነድፈው የነበሩ ዕቅዶችና የተማሪዎች የንግግር አቀራረቦች ግብ መቺነት ሲታይ አብዛኞቹ መምህራን አላማቸውን በቀጥታ ተናግረው የንግግር አቀራረቡን ያልጀመሩ ስለሆነ ዕቅዱ መሳካት አለመሳካቱ ያልታወቀው 8(75%) ክፍሎች ሲሆን 4(25%) ክፍሎች ውስጥ የቀረቡት የንግግር አተገባበሮች የተነደፈውን ዕቅድ ያሳኩ ነበሩ፡፡

በአማዛኙ በንግግር አቀራረብ ወቅት የተደረገው ምልከታ ያረጋገጠው በንግግር ወቅት መስተካከል ያለባቸው ክፍተቶች መኖራቸውን ነው፡፡

ሠንጠረዥ 6፡- የንግግር ጊዜ ተግባርን አስመልክተው መምህራን የሰጡት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ትንተና

| ተቁ | የንግግር አቀራረብ ስነ-ዘዴው | ሁልጊዜ | | አብዛኛውን ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | አልተደረገም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | በ% | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 9 | ለተማሪዎች ንግግር የተሰጠው ጊዜ በቂ ነው፡፡ | 2 | 50 | 1 | 25 | 1 | 25 | | |
| 10 | ሁሉም ተማሪዎች እኩል የንግግር እድል ማግኛታቸውን ይከታተላሉ፡፡ | 3 | 75 | | | 1 | 25 | | |
| 11 | ትኩረትዎን ሙሉ በሙሉ በተማሪዎችዎ ንግግር ላይ ያደርጋሉ? | 4 | 100 | | | | | | |
| 12 | የተማሪዎች የንግግር ወቅት ስህተቶችን ሳያልፉ በመያዝ እንዲታረሙ ያደርጋሉ፡፡ | 1 | 25 | 1 | 25 | 2 | 50 | | |
| 13 | ከስዕል፣ ከሠንጠረዥ፣ ከፎቶ ግራፍ፣ ከጋዜጣ … ንግግር አዘጋጅተው እንዲናጋሩ ያደርጋሉ፡፡ | | | | | 1 | 25 | 3 | 75 |
| 14 | ተማሪዎች ራሳቸው ርዕስ መርጠው ንግግር እንዲያደርጉ ያበረታታሉ፡፡ | 1 | 25 | 1 | 25 | 1 | 25 | 1 | 25 |
| 15 | የተነደፈው ዓላማና የተማሪዎቹ የንግግር ተግባራት ተናባው እየሄዱ እንደሆን አረጋግጠዋል፡፡ | 2 | 50 | 2 | 50 | | | | |

በሠንጠረዥ 9 የቀረበው የንግግር አቀራረብ ወይም ትግበራ ወቅትን በሚመለከት ለመምህራን ለቀረቡ ጥያቄዎች በጽሑፍ የተሰጠ ምላሽ ነው፡፡ በመጠይቁ ለተማሪዎች የንግግር መልመጃ የተሰጠው ጊዜ በቂ ነበር በሚል ለቀረበው ጥያቄ ግማሽ ቁጥር ያላቸው መምህራን ማለትም 2(50%) ሁልጊዜ ይበቃል ሲሉ 1(25%) አብዛኛውን ጊዜ ይበቃል ብለው መልሰዋል፡፡ የቀረው

1(25%) መምህር አልፎ አልፎ ይበቃል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከምልከታ የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ከዚህኛው ጋር በከፊል የሚስማማ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም የተመደበው ጊዜ ያልበቃቸውና ሳይጨርሱ ለማቋረጥ የተገደዱ ተማሪዎች ስላሉ ነው፡፡

መምህሩ የተማሪዎችን የንግግር አተገባበር ጊዜ ሰጥተው በትኩረት ከመከታተል አንፃር ለቀረበላቸው ጥያቄ 4(100%) መምህራን በተማሪዎቻቸው ንግግር ላይ እንደሚያተኩሩ መጠይቁ ያስረዳል፡፡ 100% መምህራን ክትትል ማድረጋቸው ለተግባሩ የተሰጠው ክትትል ጥሩ መሆኑን የሚያመለክት ነገር ነው፡፡ እዚህ ላይ መጠቀስና መጨመር ያለበት በክትትሉ ወቅት ለሁሉም ተማሪዎች እኩል በንግግር የመሳተፍ ዕድል መስጠቱን ለማረጋገጥ ለቀረበው መጠይቅ የተሰጠው ምላሽ ክፍተት እንዳለ ያሳያል፡፡ 1(25%) መምህሩ የተማሪዎቹን የንግግር መልመጃ አቀራረብ ሂደት የሚከታተሉት አልፎ አልፎ እንደሆነና 3(75%) መምህራን ግን ሁልጊዜ በትኩረት እንደሚከታተሉ አስረድተዋል፡፡ ታዲያ መምህራኑ አልፎ አልፎ የሚከታተሉ ከሆነ እዚያ ክፍል የተገኘበት ምክንያት ግልፅ አይደለም ማለት ነው፡፡ በሱ ክፍል ውስጥ ፈሪ ተማሪዎች አይበረታቱም፣ ጎበዞችም ጫና በመፍጠር ንግግሩን ይጫናሉ ሊባልም ይቻላል፡፡

ተማሪዎች በንግግር ወቅት የሚፈጽሙትን ስህተት 1(25%) መምህራን ሳያልፉ ሁልጊዜ የሚያርሙ ሲሆን 2(5%) አብዛኛውን ጊዜ ያርማሉ፡፡ 1(25%) ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚያርሙ ገልጸዋል፡፡ መደረግ የነበረበት ንግግሩን በማይረብሽ መልኩ ከንግግሩ በኋላ በሁሉም መምህራን መተግበር ነበረበት፡፡

ከስዕል፣ ከፎቶ፣ ከሠንጠረዥ፣ ከጋዜጣ፣ ወዘተ … ንግግር እንዲያዘጋጁ የማበረታታት ጥረት ዝቅተኛ ነው፡፡ 1(25%) አልፎ አልፎ አደርጋለሁ ያለ ሲሆን 3(75%) መምህራን ግን አናደርግም የሚል ግልፅ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የተማሪዎችን የፈጠራ አቅም የሚቀሰቅሰውን ንግግር እንዲያዘጋጁና እንዲተገብሩ የማድረግ አቅም የደከመ መሆኑን የሚያመለክት ምላሽ ነው፡፡ ተማሪዎች የሚመቻቸውን ርዕስ መርጠው ንግግር እንዲያደርጉ ያደረጉ፣ ሁልጊዜ የፈጸመ 1(25%) አብዛኛው ጊዜ ያደረጉ 1(25%)፣ አልፎ አልፎ የሚሞክሩ 1(25%) እና ፈጽሞ አድርጌ አላውቅም ያሉ 1(25%) ናቸው፡፡ ይህም ክፍተት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ የተማሪዎቀችን በራስ የመተማመን አቅም ይቀንሳል፡፡

የተማሪዎች ንግግር የተነደፈውን ዓላማ ከማሳካት አንፃርም ሲታይ የመምህራን ምላሽ የምልከታውን ውጤት የሚቃራን ሆኖ ቀርቧል፡፡ 2(50%) ከአላማ ጋር ተናበው ይሄዳሉ ሲሉ የቀሩት 2(50%) ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ተናበው ይሄዳሉ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 7፡- የንግግር ጊዜ ተግባራትን በሚመለከት ለተማሪዎች ከቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

| ተቁ | የየተማሪዎች የንግግር ሂደት ተግባራት | ሁልጊዜ | | አብዛኛውን ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | አይደረግም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 10 | ጎበዝ ተማሪዎች ውይይታችሁን እንዳይጫኑ ይደረጋል? | 28 | 25 | 42 | 37.5 | 40 | 36.7 | 2 | 0.8 |
| 11 | መምህሩ የተማሪዎችን የንግግር መልመጃ በትኩረት ይከታተላሉ? | 92 | 82 | 16 | 14.3 | 4 | 3.7 | | |
| 12 | መምህሩ የተማሪዎችን ስህተት አሳይተው ያርማሉ? | 30 | 26.8 | 50 | 44.6 | 20 | 18 | 12 | 10.6 |
| 13 | ከፎቶ፣ ከስዕል፣ ከሠንጠረዥ ወዘተ ንግግር አዘጋጅታችሁ ታቀርባላችሁ? | | | 4 | 3.7 | 90 | 81.5 | 18 | 14.8 |
| 14 | የራሳችሁን ርዕስ መርጣችሁ ንግግር ታደርጋላችሁ? | | | 10 | 8.9 | 89 | 79.5 | 13 | 11.6 |
| 15 | የምታደርጉት ንግግር ከተሰጣችሁ ዓላማ ጋር የሚስማማ ይመስላችኋል? | 4 | 3.7 | 18 | 14.8 | 80 | 72.6 | 10 | 8.9 |

ሠንጠረዥ 10 የሚነግረን በንግግር ወቅት ተማሪዎች ያጋጥማቸው የነበረውን ሁኔታ የገለጹበት የአቀራረብ ማሳያ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ጎበዝ ተማሪዎች ውይይት፣ ጭውውት፣ ክርክር ወዘተ የንግግር አይነቶችን እንዳይጫኑና የንግግር ክሂሉ ለሁሉም ተማሪዎች ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ እንዲዳረስ ለሚጠይቀው 28(25%) ተማሪዎች ሁልጊዜ ክትትል ይደረጋል ሲሉ 42(37.5%) ተማሪዎች ደግሞ አብዛኛው ጊዜ ንግግራችንን መምህራን ይቆጣጠራሉ ብለዋል፡፡

የቀሩት 40(36.7%) ተማሪዎች ደግሞ ንግግራቸውን ጎበዝ ተማሪዎች ሰፊ ድርሻ በመውሰድ ቢጫኑም የመምህራን ክትትል ዝቅተኛ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡ ጥቂት ተማሪዎች 2(0.8%) የሚሆኑት ደግሞ ፈጽሞ ክትትል አይደረግም በማለት ገልጸዋል፡፡ በዚህ መሠረት የመምህራን የተማሪዎችን ንግግር በጎበዝ ተማሪዎች እንዳይሸፈን የመቆጣጠር ጉዳይ ወጣገባነት የሚታይበት ወጥ አላመሆኑን ያሳያል፡፡ የተማሪዎችን የንግግር መልመጃ ቀርቦ በማዳመጥ ከመከታተል አኳያ ግን በአብዛኞቹ ክፍሎች ክትትል እንደሚደረግ 92(82%) ተማሪዎች ሁልጊዜ ይደረጋል በሚል የመለሱ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ይደረጋል ያሉት 16(14.3%) ናቸው፡፡ አልፎ አልፎ እንደሚደረግ የገለጹት 4(3.7%) ተማሪዎች ሲሆኑ ፈጽሞ አይደረግም ያለ የለም፡፡ በዚህ መሠረት ሁሉም የክፍል ውስጥ ንግግሮች በጎበዞች ቢሸፈኑም ባይሸፈኑም መምህራን ተከታትለው እንደሚያስፈጽሙ ያሳያል፡፡

ተማሪዎች በንግግር ወቅት ከፍርሃት፣ ከግዴለሽነት፣ ከአላማወቅ ወዘተ የተነሳ ስህተት ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡ በዚህ ወቅት መምህራን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ስህተትን ለይቶ በተለይ የተማሪዎችን የንግግር ዕድገትና ተግባቦትን የሚጎደውን ስህተት ለይተው የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡ በዚህ መሠረት መምህራን ስህተትን ሁልጊዜ ያርማሉ ያሉት ተማሪዎች 30(26.8%)፣ አብዛኛውን ጊዜ ያርማሉ ያሉት 50(44.6%) ተማሪዎች ሲሆኑ አልፎ አልፎ ያርማሉ ያሉት 20(18%) ሲሆኑ ፈጽሞ አያርሙም ያሉት ደግሞ 12(10.6%) ናቸው፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች ስህተታቸው እንደሚታረም ቢገልጹም ጥቂት ተማሪዎች ግን ከሞላ ጎደልና ፈጽሞ እንዳማይታረም አሳይተዋል፡፡ ከሌሎች የመረጃ ምንጮች ማለትም ከፎቶ፣ ከስዕል፣ ከጋዜጣ፣ ከሠንጠረዥ በማንባብና ንግግር በግልም ሆነ በቡድን በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር ይሰጣቸው እንደሆነ ከተጠየቁት መካከል ሁልጊዜ ይሰጠናል ያለ ተማሪ የሌለ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ይሰጠናል ያሉት 4(3.7%) ብቻ ናቸው፡፡ ከቀሩት መካከል አልፎ አልፎ ይሰጠናል ያሉት 90(81.5%) ሲሆኑ ፈጽሞ አይሰጠንም ያሉት ደግሞ 18(14.8%) ናቸው፡፡ ይህ የሚነግረን መምህራን የተማሪዎች ጠልቆ የማንባብ አቅም ከማጉልበት የፈጠራ አቅማቸውን እንዲጠቀሙ ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ ክፍተት እንዳለባቸው ያሳያል፡፡

የራሳቸውን ርዕስ መርጠው ንግግር የማድረግ ሁኔታን በሚመለከት ለቀረበላቸው ጥያቄም 10(8.7%) የሚሆኑት አብዛኛውን ጊዜ እንመርጣለን ያሉ ሲሆን የቀሩት 89(79.5%) አልፎ አልፎ በመረጥነው ርዕስ ዙሪያ ንግግር እናደርጋለን ብለዋል፡፡ የቀሩት 13(11.6%) ደግሞ ርዕስ መርጠን ተዘጋጅተን ንግግር አናደርግም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

የሚታደርጉት ንግግር ከትምህርት አላማው ጋር የተገናዘበ ነው ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከላይ አብዛኛቹ መምህራን የንግግርን ዓላማ እንደማይናገሩ የተገለጸውን በሚያጠናክር መልኩ 4(3.7%) ሁልጊዜ ከአላማ ጋር ይገናዘባል ሲሉ አብዛኛውን ጊዜ ይገናዘባል ያሉት 18(14.8%) ናቸው፡፡ የቀሩት 80(72.6%) አልፎ አልፎ ይገናዘባል ሲሉ 10(8.9%) ተማሪዎች ደግሞ ፈጽሞ አይገናዘብም በማለት ገልጸዋል፡፡

ከላይ የታየው ትንተና ያሳየው በንግግር ወቅት የመካከለኛና ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸው ተማሪዎች በፈጣን ተናጋሪዎች የመዋጥ፣ የተማሪዎችን ስህተት ለይተው በመያዝ መምህራን ግብረ መልስ ወዲያው ያለመስጠት ከተለያዩ ምንጮች ንግግር እንዲያዘጋጁ ያለማድረግ፣ በሚመቻቸው ርዕስ ዙሪያ መርጠው ንግግር እንዲያደርጉ ያለማድረግና አላማና ተግባር እንዲገናዘቡ ዓላማን ያለመንገር ክፍተቶች እንዳሉ የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ያሳያል፡፡

### 4.1.3. በድህረ ንግግር የንግግር አተገባበር ዙሪያ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በድህረ ንግግር ዙሪያ ከክፍል ምልከታ፣ ለመምህራንና ለተማሪዎች ከቀረቡት የጽሑፍ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡ ከላይ በቅድመ ንግግርና በንግግር ጊዜ አተገባበር ትንተና ላይ ከታየው ልዩነት በተቃራኒው በድህረ ንግግር ጊዜ የተሰባሰበው መረጃ ሦስቱ ተመሳሳይ ውጤት ተገኝቶበታል፡፡ ስለዚህ የክፍል ምልከታው ውጤት ሦስቱንም በወከለ መልኩ ይቀርባል ማለት ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 8፡- በድህረ ንግግር አተገባበር ዙሪያ በክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተቁ | የንግግር አተገባበር ተግባራት | አዎን | | አይደለም | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 16 | ከንግግር በኋላ ለተማሪዎች የጥያቄ ዕድል ተሰጥቷል? | 4 | 25 | 8 | 75 |
| 17 | ተማሪዎች የንግግር መልመጃቸውን በማረም ሂደት ተሳትፎ አድርገዋል? የጓደኞቻቸውንና የራሳቸውን ስህተት እንዲያርሙ ዕድል ተሰጥቷቸዋል? | 5 | 37.5 | 7 | 62.5 |
| 18 | መምህሩ በተማሪዎች የንግግር መልመጃ ላይ የማይታለፉ ነው ባሉት ቦታ ላይ ማስተካከያ አድርገዋል? | 6 | 50 | 6 | 50 |
| 19 | ተናጋሪ ተማሪዎች በንግግር ወቅት የተደናገሩበትን ሀሳብ መምህሩን ወይም ጓደኞቻቸውን በነፃነት ጠይቀው የማያሻሽሉት ሁኔታ ተመቻችቷል? | | | 12 | 100 |
| 20 | ስለ ንግግሩ ሂደት አስተያየት በመስጠት ንግግር የሚያደርጉበት ሁኔታ ተመቻችቷል? | 6 | 50 | 6 | 50 |
| 21 | በአጠቃላይ የንግግር ሂደቱ የተፈጠሩ ስህተቶች ተለቅመው ታርመዋል? | 8 | 75 | 4 | 25 |

ከላይ ሠንጠረዥ 11 የሚነግረን በድህረ ንግግር ወቅት ያሉትን አተገባበሮች ለማሳየት የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ከንግግር በኋላ ለተማሪዎች የጥያቄ ዕድል ስለመስጠቱ ከምልከታው የተረጋገጠው 4(25%) ሲሆን የቀሩት 8(75%) እድሉ አለመስጠቱን የምልከታው ውጤት ያመለከታል፡፡ ይህ የሚያሳየው ተማሪዎች በቡድንና በግል በጭውውት፣ በውይይት፣ በክርክር ከቀረቡት ውጪ ያሉት የሚናገሩት በጥያቄና አስተያየት አማካኝነት መሆኑ እየታወቀ ለዚሁ የተሰጠው ትኩረት 25% መሆኑ ለጉዳዩ የተሰጠውን ዝቅተኛ ትኩረት ያሳያል፡፡

ተማሪዎች የንግግር መልመጃዎቻቸውን ከማረም አንፃር ከመምህሩ በተጨማሪ የሚያደርጉትን ተሳትፎ በተመለከተ ለተጠየቀው ጥያቄ የተሰጠው ትኩረትን በተመለከተ አዎን ያሉት 5(37.5%) አይደለም ያሉት ደግሞ 7(62.5%) ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት የክፍል ውስጥ የንግግር እርማት በአብዛኛው በመምህሩ የሚሸፈን ሆኗል፡፡

ተማሪዎች ንግግር ካደረጉ በኋላ የተማሪዎችን የንግግር አቅም ሊጐዳ ይችላል ባሉት ግድፈት ላይ ማስተካከያ ያደርጉ እንደሆን በተደረገው ምልከታ አዎን ያደርጋሉ ያሉት 6(50%) ሲሆን ያላደረጉትም 6(50%) ሆኗል፡፡ እዚህም ላይ ክፍተቶች እንዳሉ የሚያሳይ ነገር አለ፡፡

በሌላ በኩል ንግግር የሚያደርጉ ተማሪዎች ለንግግር በግል በቡድንም ለክርክር፣ ለጭውውት፣ ለውይይት ወዘተ ቀርበው ሀሳብ ሲጠፋ ወይም ስህተት ውስጥ ላለመግባት ሲሉ መምህሩን ወይም ጓደኞቻቸውን የሚጠይቁበት ሁኔታ ተመቻችቷል? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ 12(100%) አልተመቻቸም የሚል ምላሽ ተመልሷል፡፡ ይህ የሚያሳየው ሰው ፍጹም ፍጥረት አይደለም፡፡ ሀሳብ በቅጽበት ሊጠፋ፣ ሊረሳ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ጓደኛን በማማከር ማስተካከያ ቢያደርጉ የጐላ ችግር የለውም፡፡ ይህ በራሱ ንግግር ነውና፡፡

ተማሪዎች በአጠቃላይ ስለንግግሩ ሂደት አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጓል በሚል ለቀረበው 6(50%) አዎን በሚል የተያ ሲሆን የቀሩት 6(50%) ደግሞ አስተያየት እንዲሰጡ አልተደረገም የሚል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ ከአንድ ትግበራ በኋላ አስተያየት መስጠትና መቀበል ተማሪዎች በአተገባበሩ ውስጥ በስሜት መሳተፍ አላመሳተፋቸውን የሚናረጋግጥበት መንገድ ነው፡፡

በአጠቃላይ በንግግሩ አተገባበር ሂደት የተፈጸሙ ስህተቶች ተለቅመው ታርመዋል? በሚል ለቀረበው ጥያቄ 8(75%) ክፍሎች እርማት ተደርጐባቸዋል፡፡ የቀሩት 4(25%) ሳይታረም እንደታለፈባቸው ምልከታው በጉልህ ያሳያል፡፡ ከሌሎቹ የንግግር አተገባበር ደረጃዎች በተለየ መልኩ የድህረ ንግግር ተግባራት የተሳኩ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

## 4.2. የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ9ኛ ክፍል አማርኛ የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ አንድ ነገር ሲፈተሽ ደግሞ ጠንካራና ደካማ ጎን ሊኖረው ይችላል፡፡ ደካማ ጎኑ የሚስተካከልበትን፣ ጠንካራ ጎኑ ደግሞ ይበልጥ የሚጠናከርበትን የመፍትሄ ሀሳብ መጠቆም ደግሞ የፍተሻው ግብ መሆን አለበት፡፡ በዚህ መሠረት ለዚህ ጥናት የመረጃ ምንጭ ሆነው ሥራ ላይ የዋሉት የክፍል ምልከታ፣ ለመምህራንና ለተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ ለምልከታ ወደተመረጡት በአራት ትምህርት ቤቶች በመሄድ ሶስት ዙር ምልከታ

ተደርጓል፡፡ በድምሩ አስረ ሁለት ጊዜ የክፍል ምልከታ ተደርጓል ማለት ነው፡፡ በሌላም በኩል ከ4 መምህራንና ከ112 ተማሪዎች በቅድመ ንግግር ተግባራት፣ በንግግር ጊዜና በድህረ ንግግር የክፍል ውስጥ አተገባበር ተግባራት ላይ መሠረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በማቅረብ መረጃ ተሰብስቦ ተተንትኗል፡፡

ትንተናው በአጠቃላይ የሚያሳየው በአብዛኛው መምህራን በዝግጅት ደረጃ አላማ ሰንቀው የሚነሱ ቢሆንም በቅድመ ንግግር ጊዜ ውስጥ ለንግግሩ መነሻ የሆነና ከንግግሩ ሊገኝ የሚችለውን ነገር የሚጠቁም ዓላማ ለንግግሩ ባለቤት ለሆኑ ተማሪዎች እንደማይነገር ጥናቱ ያሳያል፡፡ ለንግግር ተመርጦ የሚቀርበው ርዕስ የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት መነሻ ከማድረግም አንፃር ክፍተት እንደሚታይበት የክፍል ምልከታው፣ የመምህራንና የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቆች ምላሾች አሳይተዋል፡፡ ሌላው በጥንካሬው ያልታየው ጉዳይ በንግግር አተገባበር ወቅት የሚቀርቡ የውይይት፣ የክርክር፣ የጭውውት ርዕስ ጉዳዮች የተማሪዎች ዕለታዊ ህይወት በከፊል የሚነኩ መሆናቸው ነው፡፡ ተማሪዎች ሁልጊዜ ጠቀሜታ በሚገኝበት ነገር ላይ ትኩረት በማድረግ በፍቅር ይከታተሉታል፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የንግግር ርዕሶች ሀገራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ እንኳን ቢሆን ተማሪዎቹ ከመጡበት አካባቢ ጋር እንዲጣጣሙ አድርጎ ማቅረብ የመምህራን ድርሻ ቢሆንም በአብዛኛው አልተተገበረም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ፈሪና አይናፋር ለሆኑ ተማሪዎች ልዩ ትኩረት አልተሰጠም፡፡ የንግግር ቡድኖች ውስጥ ንግግር ሲያደርጉ እንኳን አልታዩም፡፡ ሰፊ ጊዜ ወስደው በመዘጋጀት ስህተትን ከመፍራት እንዲያመልጡ ልዩ ጊዜም አልተሰጣቸውም፡፡ በተለይ ከምልከታው የተገኘው መረጃ በግልጽ እንደሚያሳየው በአስረ ሁለቱም የምልከታ ክፍለ ጊዜዎች የተደረገላቸው የሚታይ ነገር የለም፡፡ ተማሪዎቹ የመለሱት መልስም ለመለማመድ የሚሰጥ ጊዜ እንደሌላ ያሳያል፡፡ በክፍል ውስጥ ፈጣን፣ መካከለኛና ቀስ ብሎ የሚማር ተማሪ ይኖራል፡፡ እነዚህ ፈሪና አይነፋር ተማሪዎች በሦስተኛው ቡድን ውስጥ ይገኛሉ፡፡ መምህራን የማስተማር ተግባራቸው ሦስቱንም ዓይነት ተማሪዎች ተዳራሽ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ በዚህ ጥናት የተደረሰበት ግን ተዳራሽ እንደሚያደርጉ የሚያሳዩ ምልክቶች በተለይ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች የሚያሳዩ ቢሆንም ተማሪዎቹን በሙሉ ተደራሽ ያደረጉ አይደሉም፡፡

ሌላው የንግግር አተገባበር ችግር ሆኖ የቀረበው በሁሉም ክፍሎችና ትምህርት ቤቶች ለማለት በሚያስደፍር መልኩ የንግግር ትግበራው በኀበዝ ተማሪዎች ቁጥጥር ስር መዋሉ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በተለይ ውይይትና ክርክር ላይ በተማሪዎቹ አወያይ፣ ተከራካሪ ሆነው የሚቀርቡት ፊት የወጡ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በውይይት ወቅት አብዛኞቹ ተማሪዎች የፈጣን

ተናጋሪ ተማሪዎችን ሀሳብ የመደገፍ ምልክት የማሳያ አንድ ሁለት ቃላት ከማለት ባለፈ ሌላ ሰፋ ያለ ጊዜ ውስደው ሲናገሩ አልታዩም፡፡ መምህራንም ተናጋሪዎችን በራሳቸው ለይተው አንተ ወይም አንቺ ተናጋር/ሪ ሲሉ አልታዩም፡፡

ሌላው የመምህራን ክፍተት ሆኖ የተስተዋለው የተማሪዎች የንግግር ስህተቶች ሳያርሙ መተው ነው፡፡ ተማሪዎቹ ራሳቸው የመለሷቸው መልሶች የሚያሳዩት ስህተት መሆን አለመሆኑን ተነግሮአቸው እንደማያወቅ ነው፡፡ ይህ ክፍተት ደግሞ ለተማሪዎቹ የንግግር ዕድገት አደገኛ መሰናክል መሆኑ ነው፡፡ በየአረፍተ ነገሩ እያስቆሙ ሳይሆን የተሰበሰበ ስህተት ከንግግሩ በኋላ በግብረ መልስ መልክ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ሌላውና ሦስቱም የመረጃ ምንጮች የተስማሙበት ከፎቶ፣ ከሠንጠረዥ፣ ከስዕል፣ ከጋዜጣ ወዘተ ንባብ ፈጠራ በታከለበት መንገድ ንግግር እንዲያዘጋጅ ፈጽሞ ያልተደረገ መሆኑ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው የተማሪዎችን ንግግር የማዘጋጀት የፈጠራ አቅም መቀስቀሻ ነገር አለመኖሩን ነው፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው መምህራንም ሆነ ተማሪዎች ለተማሪዎች በግልፅ የተነገራቸው ዓላማ ውስን ስለሆነ ዓላማውን ንግግሩ መሠረት ያድርግ አያደርግ ያለመታወቁ ነው፡፡

ተማሪዎች የሚመቻቸውን ርዕስ መርጠው ንግግር አዘጋጅተው በክፍል ውስጥ ንግግር እንዲያደርጉ ነፃነት ለተማሪዎች ከመስጠትም አንፃር ሰፊ ክፍተት እንዳለ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

ይህ ሲባል ግን ይባል የሚያሰኝ አንድም ነገር የለም ማለት አይደለም ለምሳሌ በሁሉም ክፍሎች መምህራን ለተማሪዎቹ ንግግር ጊዜ ሰጥተው በትኩረት የሚከታተሉ መሆኑ አንደኛው በጥንካሬ የተደረሰበት ተግባር ነው፡፡ በሌላም በኩል የተማሪዎችን ንግግር መምህራን ጠልቃ እየገቡ እንዲቆራረጥ አያደርጉም፡፡ ትንሽም ቢሆን ማስታወሻ በመያዝ በመጨረሻ የሚነግሩ፣ ጥንካሬና ድካሙን ሳይናገሩና ንግግሩን ሳያቆራርጡ የሚያልፉም ነበሩ፡፡

በየክፍሉ ለንግግር ቀርበው የነበሩ ርዕስ ጉዳዮች ለተማሪዎቹ ግልፅ ከሆነ ምንጭ ከተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ የተወሰዱ መሆናቸው የተደረሰበት ጠንካራ ጎን ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው መምህራኑ ከስርዓተ ትምህርቱ ውጪ ያልወጡና ከመርሀ ትምህርቱ ጋር የተገናዘበ የንግግር ትምህርት የሚሰጡ መሆኑ ነው፡፡

በመጨረሻም ምንም እንኳን የተማሪዎች ምላሾች በደካማ አመለካከት ቢፈርጁትም መምህራን ተማሪዎች በንግግር ሂደት የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ከጣልቃገቢነት በጸዳ መልኩ ማስታወሻ በመያዝ አልፎ አልፎ ስህተት መሆናቸውን ሲያሳዩ ተስተውለዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5.ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

### 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በከምባታ ጠምባሮ ዞን፣ በሀደሮ ጡንጦ ወረዳ በሚገኙ አራት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አተገባበርን ፈትሾ ደካማና ጠንካራ የሚባሉ ጉኖቹን በመለየት ጠንካራው ይበልጥ የሚጎለብትበትን፣ ደካማው የሚሻሻልበትን የመፍትሄ ሀሳብ ማስቀመጥ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ለጥናቱ በተለዩ አራት ትምህርት ቤቶች ለጥናቱ በተለዩ አንዳንድ የመማሪያ ክፍሎች ከተመረጡ አንዳንድ መምህራንና ሃያ ስምንት ተማሪዎች በድምሩ ከአራት መምህራንና አንድ መቶ አስራ ሁለት ተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አጥኚው በአራቱም ክፍሎች በሶስት ዙር በድምሩ ለአስረ ሁለት ክፍለ ጊዜዎች በክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርት ሲከናወን የክፍል ምልከታ በማድረግና አስቀድሞ ባዘጋጀው የአተገባበር መከታተያ ቅጽ ላይ በመሙላት መረጃ ሰብስቧል፡፡

ከላይ ከሁለቱም የመረጃ መሰብሰቢያዎች የተገኙ መረጃዎችን በሠንጠረዦች አዘጋጅቶ በመተንተን ለጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡ ማብራሪያው ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ጎን ለጎን በማስተያየት የቀረበ ነው፡፡

Venkantes (1997:82) በግልጽ እንደሚያስረዱት ቋንቋ የሚባል ነገር ሲነሳ መናገር ቀዳሚውን ስፍራ ይወስዳል፡፡ የሰው ልጅ ስሜቱን፣ ሀሳቡን፣ አስተያየቱን፣ ፍላጎቱን ለመግለጽ፤ ማህበራዊ ትስስርንና ወዳጅነትን ለመፍጠር መናገርን እንደመሣሪያ ይጠቀማል፡፡ ተማሪዎች መናገር ይችላሉ ሲባል እራሳቸውን ቃላዊ በሆነ መንገድ የመግለፅ ችሎታና ፍሰት ተጠብቆ፣ የሀሳብ መቆራረጥ ሳይኖር በተገቢው መንገድ መናገር ሲችሉ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በዚህ ጥናት ግኝት ሆነው ከቀረቡት መካከል አብዛኞቹ መምህራን የተማሪዎችን የመናገር መልመጃዎች አላማ የማይናገሩ መሆኑ ነው፡፡ ከንግግራቸው መነሻ የሚደርሱበት ካልተነገራቸው በፍላጎት የመናገር ነገር የቀዘቀዘ ይሆናል፡፡ ውጤቱ የሚያሳየውም ይህንኑ ነው፡፡ የንግግር ሂደቶቹም ተማሪዎቹ ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ የማያመለክቱና የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ ተመርኩዘው የቀረቡትን እንዳለ ተቀብለው እንዲተገብሩ የተደረገ በመሆኑ ተማሪዎች ዘንድ የመሰላቸት ሁኔታ ታይቷል፡፡ ስለዚህም ግዴለሽነት ሲታይባቸው

ተስተውሏል፡፡ ለመናገር የሚፈሩና አይናፋር ተማሪዎችን ጊዜ ወስደው እንዲዘጋጁ የማድረግ ተግባር ያልተፈጸመ በመሆኑም ንግግሩ ሁላቀፍነት የሌለው በፈጣንና በጎበዝ ተማሪዎች ቁጥጥር ስር ሲውል ተስተውሏል፡፡

በአጠቃላይ የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት መምህራን (የንግግር ክሂል ትግበራውን አስበውበትና ጊዜ ወስደው የተማሪዎችን በራስ የመተማመንና የመናገር ፍላጐት በሚቀሳቅስ መልኩ ያላዘጋጁት ዓላማ እንኳን በትክክል ያልተናገሩበት ስለሆነ የንግግር ፍላጐትን የማይቀሳቅስ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተቃራኒው ስርዓተ ትምህርቱን በአግባቡ ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ለክፍል ትምህርቱ መሠረት የሆነውን የተማሪ መጽሐፍ የተጠቀሙ መሆኑና በየክፍለ ጊዜ በአካል በመገኘት ንግግሩን መምራት መቻላቸው እንደ ጥንካሬ የሚወሰድ ተግባር ነው፡፡ ሆኖም የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበር ጊዜ ወስደው ሲሰራ አልታዩም፡፡ ስለዚህ ከላይ ከቀረበው ሁኔታ የምንረዳው የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበርና ፍላጐትን ለመቀስቀስ መምህራን በቂ ጊዜ ወስደው ዓላማቸው ግልፅ በማድረግና ከተማሪዎቻቸው ጋር በመጋራት ሥራውን እንዳላከናወኑት ነው፡፡

## 5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች

የዚህ ጥናት መነሻ በክፍል ውስጥ ለንግግር ክሂል መዳበር ሳንካ የሆኑ ነገሮችን ለይቶ በማውጣት ለወደፊቱ የሚሻሻሉበትን የመፍትሄ ሀሳብ መሰንዘርና ጠንካራ ጐኖቹ ይበልጥ የሚጎለብቱበትን ሀሳብ ማቅረብ ነው፡፡

ስለዚህ ጥናቱ ያቀረባቸውን ጥያቄዎችና የደረሰባቸውን ድምዳሜዎች መሠረት በማድረግ የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡

- ሁሉም መምህራን የአንድን ንግግር አላማ በመለየት ከንግግር ዝግጅቱና አቀራረቡ በፊት ለተማሪዎች የሚገለጽበት ሁኔታ ቢመቻች፣
- ተማሪዎች ንግግርን በቀጥታ ከመጀመራቸው በፊት የዝግጅት ጊዜ ቢሰጣቸው፣
- ሁሉም ተማሪዎች በንግግሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ አይናፋርና ፈሪ ለሆኑ ተማሪዎች የልምምድ ጊዜ የሚሰጥበት ሁኔታ ቢመቻች፣
- ለተማሪዎች ለንግግር የሚመረጡ ርዕስ ጉዳዮች የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት መሠረት በማድረግ ባላቸው ላይ የሚጨምሩ መሆኑ ቢረጋገጥ፣

- ተማሪዎች ንግግር ከመጀመራቸው በፊት የአካሄድ ቅደም ተከተል የሚያሳይ መመሪያ ቢሰጥ፣ ሲጨርሱም ሌላ የንግግር ዕድል ይሆን ዘንድ የአስተያየትና የጥያቄ ዕድል ቢመቻች፣

# ዋቢ ፅሑፎች


ማረው አለሙ፡፡ (1998)፡፡ የአማርኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ዘዴ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ማረው አለሙ፡፡ (2003)፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ማስተማር ዘዴ፡፡ ሁለተኛ ዕትም፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

መዝገባ ገ/ሚካኤል፡፡ (2008)፡፡ በመቐለ ከተማ የ10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባባር፡፡ በመቐለ ዩኒቨርሲቲ፣ (ያልታተመ)፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡ በሥነ-ፅሑፍ ቋንቋ ማስተማር፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (2007)፡፡ በሥነፅሑፍ ቋንቋ ማስተማር፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ቅድስተ ማርያም ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፡፡ (2006)፡፡ "ስነ-ጹሑፍ አማርኛ ቋንቋ ማስተማር"፡፡ አዲስ አበባ፣ ቅድስተ ማርያም ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፡፡

ተስፋዬ ሽዋዬ፡፡ (1981)፡፡ "ስነ ልሳንን እና ቋንቋን ማስተማር" የቋንቋዎች እና ጥናት ተቋም፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

አብርሃም ገ/ዮሐንስ፡፡ (2003)፡፡ በአፋር ክልል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና አቀራረብ፡፡ አዲስ አበባ (ያልታተመ)

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2009)፡፡ የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡ 3ኛ ዕትም፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጌታቸው በለጠ፡፡ (2004)፡፡ የጥበባት ጉባኤ፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

Bygate, M.(1987). Speaking Oxford; Oxford University Press.

Byrne, D. (1976). Teaching Oral English, London; Longman.

Byrne, D. (1987). Techniques for Class Room Interaction. London: Longman Group UK Limtied.

Harmer, J. (1991). The practice of Language, London: Long man Group UK Lmited.

Harmer, J. (2007). How to Teach English. London: Longman. Lewis & Sick (1993).

Kyriacou, C.(1998). Essential of Teaching Skills (2nd,) London: Nelson Thornes. Larsen-Freeman.

MCDonough, J. and Shaw, C. (1995). Materials and Methods in ELY: A Teacher's Guide. Oxford: Blackwell Publishers Ltd.

Nunan, D. (1991). Designing Tasks for the Communicative Classroom. Combridge: CUP

Nunan, D. (2003). Language Teachinge Methodology. New York: Prentice Hall.

Richards, J.C. & Rogers, T.S. (1989). Rivers, W.M. (1987). Interactive Language Teaching. Cambridge: Cabrige University Press.

Sesnan. (1997). How to Teach English. Oxford: cup.

Tricia Hedge. (1996). Teaching and Learning in the Language Class Room. Oxford University press.

Ur.P. (1996). Course in Language Teaching Practice and Theory. Cambridge: CU.

Venkants Warn,S.(1997).Principle of Teaching English. New Delghli: Vikas Publishing House PUTLTD.

**አባሪ አንድ**

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሥነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር**

**የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ**

**(በከምባታ ጠምባሮ ዞን ሀደሮ ጡንጦ ወረዳ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)**

**<u>የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅጽ</u>**

የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አተገባበርን ለመመልከት የሚያስችል የአተገባበር መከታተያ ቅጽ ነው፡፡

የትምህርት ቤቱ ስም ________________________________

ምልከታው የተደረገበት ቀን ________________________________

ምልከታ የተደረገበት ክፍል ________________________________

ምልከታው የተደረገበት ሰዓት ________________________________

ምልከታው የተደረገበት ክፍለ ጊዜ ________________________________

የዕለቱ የንግግር ክሂል ርዕስ ጉዳይ ________________________________

የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ምልከታ ቅጽ ላይ የተጠቀሰው ተግባር ተፈጽሞ ከሆነ “አዎን” በሚል ትይዩ የ “X” ምልክት፣ አልተፈጸመ እንደሆነ “አይ” ከሚል ትይዩ የ “X” ምልክት በማድረግ ቅጹ ይሞላል፡፡

| ተ.ቁ | የክፍል ውስጥ የንግግር አተገባበር | አዎን | አይ |
|---|---|---|---|
| ሀ. | **ቅድመ ንግግር ተግባራት** | | |
| 1 | የንግግር መልመጃ ትግበራ ከመጀመሩ በፊት አላማው በትክክል ተገልጾ ነበር? | | |
| 2 | ለንግግር የቀረበው ርዕስ ለተማሪዎች ግልፅ ነበር? | | |
| 3 | ለንግግር የተመረጠው ርዕስ የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ያገናዘበ ነበር? | | |
| 4 | የንግግር አተገባበር ቅደም ተከተሉ በቅድሚያ ተገልጾ ነበር? | | |
| 5 | ለንግግሩ የማያሻማ ግልፅ መመሪያ ተሰጥቶ ነበር? | | |
| 6 | ለንግግሩ የቀረበው ርዕስ የተማሪዎቹን ዕለታዊ ህይወት የሚያሳይ ወይም ከክፍል ውጭ ያለውን ሁኔታ የሚያመለክት ነበር? | | |
| 7 | ፈሪና አይናፋር ባጠቃላይ ለተማሪዎች የንግግር መለማመጃ በቂ ጊዜ ተሰጥቶ ነበር? | | |
| ለ. | **የንግግር ጊዜ ተግባራት** | | |
| 8 | ለንግግር የተመደበው ጊዜ ለንግግሩ በቂ ነበር? ተገድቦ ነበር? | | |
| 9 | ንግግሩ በጎበዝ ተማሪዎች ተፅዕኖ ስር እንዳይወድቅ ጥንቃቄ ተደርጓል? | | |
| 10 | መምህሩ የተማሪዎችን ንግግር በትኩረት ይከታተሉ ነበር? | | |
| 11 | መምህሩ በንግግር ወቅት ተማሪዎች ስህተት ሲፈጽሙ ተከታትለው ያርማሉ? | | |
| 12 | ከሚታዩ ወይም ከሚነበቡ ወይም ከተጎበኙ ነገሮች ላይ የተዘጋጀ ንግግር ቀርቦ ነበር? | | |
| 13 | ንግግሩ ተማሪዎች በመረጡት ርዕስ ዙሪያ ያጠነጠነ ነበር? | | |
| 14 | የንግግሩ አካሄድና የተነደፈው አላማ አብረው የሚሄዱ ናቸው? | | |

| ተ.ቁ | የክፍል ውስጥ የንግግር አተገባበር | አዎን | አይ |
|---|---|---|---|
| ሐ. | **ድህረ ንግግር ተግባራት** | | |
| 15 | ለአድማጭ ተማሪዎች በጥያቄ አማካኝነት የመናገር ዕድል ተሰጥቷል? | | |
| 16 | የንግግር መልመጃው ዕርማታ/ማስተካከያ/ ተማሪዎችን ያሳተፈ ነበር? | | |
| 17 | ተማሪዎች ስህተታቸው እርስ በርስ እንዲተራረሙ ዕድል ተመቻችቷል? | | |
| 18 | መምህሩ በተማሪዎች ንግግር ላይ አላስፈላጊ ነው ያሉትን ማሻሻያ አድርገዋል? | | |
| 19 | ተናጋሪ ተማሪዎች ያልገባቸውን የሚጠይቁበት አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር? | | |
| 20 | በንግግር ሂደቱ የተከሰቱ ስህተቶች በመጨረሻ ባይታለፉ ተለቅመው ታርመዋል? | | |
| 21 | ስለ ንግግሩ ሂደት ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጓል? | | |

## አባሪ ሁለት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሥነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

## የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ

## (በከምባታ ጠምባሮ ዞን ሀደሮ ጡንጦ ወረዳ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)

**<u>በተመረጡ የ9ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ</u>**

ወድ የ_______________________________________ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህር፣ ይህ የጽሑፍ መጠይቅ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን እንዴት እየተገበሩ እንዳለ ለመፈተሽ የተዘጋጀ ነው፡፡ ከዚህ የጽሑፍ መጠይቅ የሚገኝ መረጃም የተጀመረው ጥናት ለማሳካት ወሳኝ መረጃ የሚገኝበት ነው፡፡ ይህ ጥናት የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ የሙያው ባለቤት የሆኑ መምህራን ድጋፍ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ስለዚህ እርስዎ መጠይቁን በሙሉ ነፃነት በመሙላት ለጥናቱ ስኬት ሙያዊ ድጋፍ እንዲያደርጉ በአክብሮት እየጠየቅሁ ለትብብርዎ በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>አጠቃላይ መረጃ</u>

ቀጥሎ ለቀረቡት መጠይቆች ተገቢውን መልስ በክፍት ቦታ በመሙላት ይመልሱ

1. ፆታ ___________________________
2. የትምህርት ደረጃ __________________
3. የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት ____________________________
4. የሚያስተምሩት ትምህርት ________________________________
5. የአገልግሎት ዘመን __________________________________
6. የአማርኛን በማስተማር የያዙት አገልግሎት ____________________

## ክፍል ሁለት

ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በሠንጠረዡ ከቀረቡላቸው መልሶች መካከል በመረጡት ትይዩ የ "X" ምልክት በማድረግ ይለዩ፡፡

| ተ.ቁ | ዝርዝር የመምህሩ ተግባራት | ሁልጊዜ | አብዛኛውን ጊዜ | አልፎ አልፎ | አላደረጉም |
|---|---|---|---|---|---|
| ሀ. | **ቅድመ ንግግር ተግባራት** | | | | |
| 1. | የንግግር መልመጃ ከመጀመሩ በፊት የንግግሩን አላማ ይናገሩ ነበር? | | | | |
| 2 | ለተማሪዎች ግልጽ የንግግር ርዕስ መርጠው ያዘጋጁ ነበር? | | | | |
| 3 | ለተማሪዎች የቀደመ ዕውቀት ተመጣጠኝ ርዕስ መርጠዋል | | | | |
| 4 | ከንግግር ትምህርት በፊት የንግግሩ አካሄድ ቅደም ተከተል ይናገሩ ነበር? | | | | |
| 5 | ለንግግር መልመጃው የሰጡት መመሪያ አሻሚ ያልሆነ ነው? | | | | |
| 6 | ለንግግር የመረጡት ርዕስ የተማሪዎችን ዕለት በዕለት ህይወት የሚያሳይ ነው? | | | | |
| 7 | ለተማሪዎች ንግግር መለማመጃ በቂ ጊዜ ይሰጣሉ? | | | | |
| 8 | አይናፋርና ፈሪ ተማሪዎች እንዲለማመዱ ሁኔታዎችን አመቻችተዋል? | | | | |
| ለ. | **የንግግር ጊዜ ተግባራት** | | | | |
| 9 | ለተማሪዎች የንግግር መልመጃ የሰጡት ጊዜ በቂ ነበር? | | | | |
| 10 | ንግግሩ በጉበዝ ተማሪዎች እንዳይሸፈን ክትትል ያደርጉ ነበር? | | | | |
| 11 | የተማሪዎች ንግግር ትኩረት ሰጥተው ይከታተላሉ? | | | | |

| ተ.ቁ | ዝርዝር የመምህሩ ተግባራት | ሁልጊዜ | አብዛኛውን ጊዜ | አልፎ አልፎ | አላደረጉም |
|---|---|---|---|---|---|
| 12 | በንግግር ተማሪዎች የሚፈጽሙትን ስህተት ተከታትለው ይገስፃሉ? | | | | |
| 13 | ከስዕል፣ ከፎቶ፣ ንግግር እንዲያዘጋጁ አድርገው ያውቃሉ? | | | | |
| 14 | ተማሪዎች ርዕስ መርጠው ንግግር እንዲያደርጉ ዕድል ይሰጣሉ? | | | | |
| 15 | አላማዎትና የንግግሩ ተግባሩ አብረው መሄዳቸውን አረጋግጠዋል? | | | | |
| ሐ. | **ድህረ ንግግር ተግባራት** | | | | |
| 16 | አድማጭ ተማሪዎች ጥያቄ የመጠየቅ ዕድል ተሰጥቷቸው ነበር? | | | | |
| 17 | ተማሪዎች የንግግር መልመጃቸውን የማረም ዕድል እንዲያገኙ አድርገዋል? | | | | |
| 18 | ዕርስ በርስ ስህተታቸውን እንዲተራረሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ? | | | | |
| 19 | በተማሪዎች የንግግር መልመጃ ላይ አስፈላጊ ማሻሻያ ያደርጋሉ? | | | | |
| 20 | ተናጋሪ በንግግራቸው ወቅት አደናጋሪ የሆነ ነገር ቢያጋጥማቸው ጠይቀው የማስተካከል ዕድል ተዘጋጅቶላቸው ነበር? | | | | |
| 21 | በንግግሩ ሂደቱ የተከሰቱ ስህተቶች ሳይታለፉ የሚታረሙበት ሁኔታ አለ? | | | | |
| 22 | ስለ ንግግሩ ሂደት ተማሪዎች አስተያየት የሚሰጡበት ሁኔታ ተመቻችቷል? | | | | |

አባሪ ሦስት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሥነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ

(በከምባታ ጠምባሮ ዞን ሀደሮ ጡንጦ ወረዳ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)

<u>በተመረጡ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ</u>

## <u>ውድ ተማሪዎች</u>

ይህ የጽሑፍ መጠይቅ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመናገር ክሂል አተገባበር በክፍል ውስጥ የሚቀርብበትን ሁኔታ ለመፈተሽ የተዘጋጀ ነው፡፡ ትክክለኛ መልስ መስጠት ጥናቱን ስኬታማ የማድረግ ድርሻው ከፍተኛ ነው፡፡ ስለዚህ ትክክለኛ መልስ በመስጠት ስለምትተባበሩኝ በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

1) የትምህርት ቤቱ ስም ______________________________

2) ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ወረዳ ______________________

3) የተማሪው የክፍል ደረጃ ___________________________

4) የተማሪው ፆታ    ወንድ ☐    ሴት ☐

## ክፍል ሁለት

ቀጥለው የቀረቡትን ባለህ/ሽ ዕውቀት መሠረት ከቀረቡት አራት አማራጮች በመረጥከው/ሽው ስር ባለው ክፍት ቦታ የ “X” ምልክት በማድረግ መልስ/ሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ሁልጊዜ ያቀርባሉ | አብዛኛውን ጊዜ | አልፎ አልፎ | አያቀርቡም |
|---|---|---|---|---|---|
| ሀ. | **ቅድመ ንግግር ተግባራት** | | | | |
| 1 | ንግግር ከመጀመራችሁ በፊት መምህሩ ግልፅ አላማ ያቀርባሉ? | | | | |
| 2 | መምህሩ የሚመርጡት ርዕስ ለናንተ ግልፅ ነበር? | | | | |
| 3 | የተመረጠው ርዕስ ካላቸው የንግግር ችሎታ ጋር ተመጣጠኝ ነበር? | | | | |
| 4 | ንግግር ከመጀመራችሁ በፊት የንግግር አካሄድ ቅደምተከተል የሚያሳይ ግልፅ መመሪያ ይሰጣችኋል? | | | | |
| 5 | ለንግግሩ የሚሰጠው መመሪያ አሻሚነት የለውም? | | | | |
| 6 | ለንግግር የሚመርጡት ርዕስ የዕለት ተዕለት ህይወታችሁን የሚያሳይ ነበር? | | | | |
| 7 | ለንግግር መለማመጃ በቂ ጊዜ ይሰጣችሁ ነበር? | | | | |
| 8 | ለንግግር የሚመደበው ጊዜ ለንግግር መልመጀው በቂ ነበር? | | | | |
| 9 | በመካከላችሁ ለሚገኙ አይናፋርና ፈሪ ተማሪዎች ንግግር እንዲለማመዱ ሁኔታዎች ይመቻቹ ነበር? | | | | |
| ለ. | **የንግግር ጊዜ ተግባራት** | | | | |
| 10 | ጎበዝ ተማሪዎች ንግግሩን እንዳይሸፍኑት መምህሩ ክትትል ያደርጋሉ? | | | | |
| 11 | መምህሩ የተማሪዎችን ንግግር በትኩረት ይከታተላሉ? | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ሁልጊዜ ያቀርባሉ | አብዛኛውን ጊዜ | አልፎ አልፎ | አያቀርቡም |
|---|---|---|---|---|---|
| 12 | የፈጠራ አቅም የሚጠይቅ ርዕስ ተዘጋጅቶ ይሰጣችሁ ነበር? | | | | |
| 13 | መምህሩ ተማሪዎች ስህተት ሲፈጽሙ እግር በእግር እየተከታተሉ አይደረግም/አይባልም በማለት ይገስፃሉ? | | | | |
| 14 | ከፎቶ፣ ከስዕል፣ ከሠንጠረዥ በማየት ንግግር እንድታዘጋጁ ይደረጋል? | | | | |
| 15 | ርዕስ መርጣችሁ ንግግር የምታደርጉበት ነፃነት ይሰጣችኋል? | | | | |
| 16 | መምህሩ የሰጡኣችሁ አላማ ጋር ንግግራችሁ የሚስማማ ይመስላችኋል? | | | | |
| ሐ | **ድህረ ንግግር ተግባራት** | | | | |
| 17 | አድማጭ የሆኑ ተማሪዎች የጥያቄ ዕድል እንዲያገኙ ተደርጐ ነበር? | | | | |
| 18 | የራሳችሁ የንግግር መልመጃ የማተራረም ዕድል ተሰጥቷችሁ ያውቃል? | | | | |
| 19 | ተናጋሪዎቹ በራሳቸው ንግግር ላይ እያሉ የተሳሳቱትን የማረም ዕድል ይቀርብላቸዋል? | | | | |
| 20 | በንግግር መልመጃችሁ ላይ አስፈላጊ የሆነ ማሻሻያ ይደረጋል? | | | | |
| 21 | በንግግራችሁ ወቅት የሚፈጸሙ ስህተቶች ሳይታለፉ ይታረማሉ? | | | | |
| 22 | በመምህሩ የሚቀርቡ ንግግራችሁ የሚያበረታቱ ግብረ መልሶች /ጎበዝ፣ በርታ፣ በጣም ጥሩ …/ አሉ? | | | | |
| 23 | ስለንግግሩ ሂደት አስተያየት እንድትሰጡ ይደረጋሉ? | | | | |